
# እውቀት




ከጳውሎስ ኞኞ

# እውቀት

ከጳውሎስ ኞኞ

# ማውጫ


የሰው ዘር ........ 11

መቼ ተፈጠረ። ........ 11

ርዝማኔ፤ ........ 11

ድንክዬ፤ ........ 12

ክብደት፤ ........ 12

አወላለድ! ........ 13

የተጣበቁ ልጆች፤ ........ 14

መንታ፤ ........ 14

ጥፍር ........ 15

ጢም ........ 15

ሪዝ ........ 15

ጠጉር ........ 16

ድምፅ፤ ........ 16

እንቅልፍ፤ ........ 16

ጾም፤ ........ 17

የረሀብ አድማ ........ 17

መታፈን ........ 17

እጅን እንደ እግር ........ 17

ማልመድ ........ 18

ጋብቻ ........ 18

ሀብት ........ 20
ደሞዝ ........ 20
ታይፒስት ........ 21
ሩጫ ........ 21
ማራቶን ........ 22
ዳንስ ........ 24
የከረቦ አመታት ........ 24
ፒያኖ ........ 25
ንግግር ........ 25
ትንባሆ ........ 26
ዓለም ........ 27
መሬት ........ 27
ውቅያኖስ ........ 27
ከዋክብት ........ 28
ፀሐይ ........ 29
ወንዝ ........ 29
ፏፏቴ ........ 30
ሐይቅ ........ 30
የተከፋፈሉ ዓለማት፤ ........ 30
የመሬት መንቀጥቀጥ፤ ........ 31
ግዛት ........ 31

ሕዝብ ........ 32
ግራኝ ........ 32
ሃይማኖት ........ 33
ቋንቋ ........ 33
ፊደላት ........ 34
ቁጥር ........ 34
ዓይን ........ 35
ጦርነት ........ 36
ወህኒ ቤት ........ 37
ንግድ፤ ........ 37
ኩባንያ ........ 37
ትርፍ ........ 38
ኪሣራ ........ 38
ሆቴል ........ 38
የመጽሐፍት ሱቅ፤ ........ 39
የጫማ ሱቅ፤ ........ 40
ጋራዥ ........ 40
አዳራሽ ........ 40
እስታዲዮም ........ 40
ናይት ክለብ፤ ........ 41
ፎቶ ግራፍ፤ ........ 42

መጠጥ፤ .......... 43
ጋዜጣ .......... 43
መጻሕፍት .......... 43
ማኅበር .......... 44
የሠራተኞች ማኅበር .......... 44
ሕንፃ .......... 44
መገናኛ፤ .......... 46
አኤሮፕላን .......... 46
ጉዞ .......... 47
ጣቢያ .......... 47
ባቡር .......... 48
ጣቢያ .......... 48
መኪና .......... 49
አውቶሞቢል .......... 49
አውቶብስ .......... 50
ካሚዮን .......... 50
መንገድ .......... 51
የመኪና ብዛት፤ .......... 51
ብስክሌት .......... 51
ስልክ .......... 52
ብዛት .......... 53

ፖስታ ........................................ 53
ግብርና። ........................................ 54
እርሻ........................................ 54
ከብት........................................ 54
እንስሳትና አራዊት ........................................ 55
በግ........................................ 55
ፍየል ........................................ 55
አሳማ........................................ 56
ውሻ ........................................ 56
ላም ........................................ 57
ዶሮ ........................................ 57
ፈረስ........................................ 57
ድመት ........................................ 58
ዝሆን........................................ 58
ቀጭኔ ........................................ 59
ነብር........................................ 59
አዞ ........................................ 60
ኤሊ ........................................ 60
አባብ ........................................ 61
እንቁራሪት........................................ 62
አሣ ........................................ 62

ሽረሪት ........................................................... 63
ጉንዳን........................................................... 63
ቁንጫ........................................................... 63
ቢራቢሮ ........................................................... 64
ጫካ (ዱር) ........................................................... 64
ዛፍ........................................................... 64

# የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ
# ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች

## 2ኛ ተሰሎንቄ 3/17

አሁንም እንዴት ከረማችሁ እላችኋለሁ። ክብሩ ይስፋ ለመድኃኔ ዓለም እኔ እንዳለሁ አለሁ።

ዕውቀት ያልኳትን ይህችን መጽሐፈ አቀረብኩ። የማልክደው ነገር ጥሩ ሳትሆን አትቀርም ብዬ አምንባታለሁ። በተራቀቀ አማርኛ ታስደስታለች ብዬ ሳይሆን ለማወቅ የሚፈልጉ ቢኖሩ ታሳውቃለች ብዬ ነው።

ባልናገረውም ከመጽሐፍ መተርጐሜን ታውቃላችሁ። ከብዙ መጻሕፍት ነው ያጠረቃቀምኳት። ብዙውን ነገር ደግሞ ትቼዋለሁ። ያገሬ ገበሬ ወይም የአካባቢውን የሚያውቀው ገበሬ አንዳንድ ነገሮችን እንዲያውቅ ትረዳዋለች ብዬ ያዘጋጀኋት። ለዚህ ነው ብዙውን በገር ትቼ ሊገባው የሚችለውን ብቻ ያጠራቀምኩት።

ለዚሁም ቢሆን እያፈርኩ ይሁን ይሁን ብዬ እንዲታተም የፈረድኩበት አለ። ለምሳሌ የምድርን ዕድሜ ስገልጽ እፍረት ይዞኛል። በኛው አቆጣጠር ገና ስምንት ሺህ ዓመታት ያልሞላ በመሆኑ ነው። ይህን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮች አሉ። ብዙም አስደናቂ ታሪኮች አሉበት። ሊያስደንቅ የሚችለው ሳይንቲስቶች ወይም ሊቃውንቶች አይሆንም የሚሉት ነገር ሆኖ መገኘቱ ነው።

ለተራ ሰው እንዲገባው በማለት አንዳንድ የምንዛሪ ለውጦች አድርጌአለሁ። ፈረንጆቹ ሦስት ፊት የሚሉትን ወደ ሁለት ክንድ መንዝሬዋለሁ። ሁለቱን የሚዛን ፓውንድ ወደ አንድ ኪሎ መነዘርኩት። አንዱን ቶሎ 1016 ኪሎ እያደረግሁ ሠራሁት። አርባውን ኤክር አንድ ጋሻ ብያለሁ። ሌሎችም የምንዛሪ ለውጦች አሉ። በመጽሐፊቱ ውስጥ ያለው የዓመት ምሕረት አቆጣጠር ግን በሙሉ በፈረንጅኛ ነው፡

የሶቪዬት ሕብረት በማለትም ፈንታ መስኮብ ያልኩበት ብዙ ቦታ ነው። ቂል ሆኜ ሳይሆን አውቄ ነው። ብዙው የኛ አገር ሰው የለመደው መስኮቦች የሚለውን በመሆኑ ነው። ጥሬውን ትርጉም ማቅረብ ነበረብህ የምትሉኝ ብትኖሩ የፈለጋችሁትን በሉኝ እንጂ አልሚገትም።

ብዙ ነገሮች ትቻለሁ ብያለሁ። በኔ አስተያየት ያን ገበሬ ወንድሜን ብዙ ከማስቸገር በሚያውቀው መነጋገር ይበጃል ብዬ ነው። ዝብዝብ አበዛሁ እንጂ ባጭር አነጋገር አጭር ማወቂያ ትሁ ብዬ ነው። እርግጥ አዋቂቆች የማያውቁት ብዙ ነገር እንዳለባት ይገባኛል። ያም ቢሆን በምጽፋት ጊዜ በአእምሮዬ ውስጥ የነበሩት የኔ ቢጤዎች ያልተማሩት ወገኖቼ ነበር። ለነሱ ነው አይዘጋጀኋት። ግን እግረ መንገዱን ማንም የፈለገ ሁሉ ቢጠቀምባት ግድ የለኝም።

ደህና እንሁን።

# የሰው ዘር

## መቼ ተፈጠረ።

የዓለም ሊቃውንት እንደሚሉት ሰው የተፈጠረው ከሰባ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ነው። ሰው ኑሮውን ለማሻሻል የጀመረበት ጊዜ ሊቃውንቶች ሲናገሩ ከ12 ሚሊዮን አሥር ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ ነው።

ሊቃውንት የሰው ዘር ከብዙ ዓመታት በፊት መኖሩን ያወቁበትን ማስረጃዎች ያቀርባሉ። በ1959 ዓ.ም ሐምሌ 17 ቀን የሰው ዘር አጥኒ ጓድ የሆኑት ወይዘሮ ሜሪ ሊኪ በታንጋኒካ ውስጥ ኦልድባይ ጐርጌ የተባለ ቀበሌ አንድ የሰው ጭንቅላት ከነጥርሶቹ አግኝተዋል። ያ የተገኘው የሰው ጭንቅላት ከአንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ ዓመታት በፊት በሕይወት የነበረ ሰው መሆኑ ተረጋግጧል።

በ1961 ዓ.ም በኬንያ ውስጥ ዶክተር ሎይስ ያገኙት የሰው ጭንቅላት ተመርምሮ አሥራ አራት ሚሊዮን ዓመታት ዕድሜ እንዳለው ታውቋል። በቻይና ውስጥ የተገኘው የሰው አፅም ስምንት ክንድ ወይም 12 ጫማ ርዝመት ስላለው ከ500.000 ዓመታት በፊት የነበሩት ሰዎች ረጃጅሞችና ግዙፎች መሆናቸውን ተረጋግጧል።

መጽሐፊቱ ጠቅላላ የሳይን ዕውቀትን የምትገልጽ ባለመሆንዋ ባጭሩ ለማወቅ ያህል የሰው አፈጣጠርና ታሪክ በዚህ ያበቃል። አሁን ወደ ቅርቡ ዘመን እንመለስ።

## ርዝማኔ፤

ማሪን ወዴ የተባለች ጀርመናዊት ሴት ቁመናዋ ስድስት ክንድ ነበር። ታላላቅ የሆኑ ነገሮች በማስታወሻ መያዝ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ማሪን ወዴን በቁመት የምትወዳደር ሴት አልተገኘችም። ማሪን ቤንኬንደርፍ በተባለ አምባ በ1866 ዓ.ም ተወለደች። የስድስት ክንድ ርዝማኔ ያገኘችው በተወለደች በ16 ዓመቷ ነው። ማሪን በቶሎ አድጋ ቶሎ ሞተች። በተወለደች በ17 ዓመትዋ በ1883 ዓ.ም በበርሊን ከተማ አረፈች።

በቅርቡ በ1974 ዓ.ም ደሎሪስ ፑላርድ የተባለች ልጅ በሉዝያና ከተማ ተወልዳ ነበር። በተወለደች በሰባት ዓመት ዕድሜዋ ቁመትዋ አምስት ክንድ ተኩል ደረሰ። ማሪን ወዴን ለመወዳደር በደረሰችበት ጊዜ ሞት ወሰዳት።

## ድንክዬ፤

በ1707 የተወለደው ጆርጅ ቡፊን የተባለው ድንክዬ በቁመቱ እጥረት የታወቀ ነበር። በተወልደ በሰላሣ ዓመቱ የቁመቱ ርዝመት አንድ ክንድ ብች ነበር። ጆርጅ ቡፊን ከሱ በፊት የነበረውን የጀፍሪ የድንክዬነት ሪኮርድ (ብልጫ) አሻሽሏል። ጀፍሪ ሁሶ በ1619 ዓ.ም በእንግሊዝ ሀገር አክህም በተባለ ከተማ የተወለደ የታወቀ ድንክዬ ነበር። ጀፍሪ በተወለደ በሰላሣ ዓመት ዕድሜው ቁመቱ አንድ ክንድ ከጋት ነበር። እያደር እያደገ መሄድ ጀመረ። በ1682 ዓ.ም ሲሞት ቁመቱ ሁለት ክንድ ከስንዝር ነበር።

ዎልተር ቦኢንግ የተባለ ድንክዬ ደግሞ በተወልደ በ48 ዓመቱ በ1955 ዓ.ም በየካቲት ወር ሞቶ በጀርመን ሀገር በድልሜንሆርስት ሲቀበር ቁመቱ ሁለት ክንድ የማይሞላ ነበር። በዓለም ከተፈጠሩ ድንክዬዎች ሁሉ እስካሁን ድረስ ቀደም ብለን ያወራነውን ጆርጅ ቡፊን በድንክዬነት የሚወዳደረው አልተገኘም።

## ክብደት፤

በኢሊኖይስ ከተማ የተወልደው ሮበርት ኧርል ከባድ ሰው ነበር። የተወለደ ዕለት አምስት ኪሎ ተኩል ይመዝን ነበር። በተወልደ በአሥር ዓመቱ 189 ኪሎ መዘነ። በ1958 ዓ.ም ለመጨረሻ ጊዜ ተመዝኖ የሮበርት ክብደት 530 ኪሎ ሆነ።

በ1958 ዓ.ም ሐምሌ 10 ቀን በተወልደ በ30 ዓመቱ በኢዋ ግዛት በብሬን ከተማ ሞተ። የመቃብር ሣጥን ተሠራለት። በስንት ድካም ሬሳው ከሣጥኑ ውስጥ ተከተተ። ሬሳ አንሺዎች ሣጥኑን ከነሬሳው ለመሸከም ቀርቶ ለማነቃነቅ አቃታቸው። የዚያን ጊዜ ክብደቱ 550 ኪሎ ነበር። ሬሳው በከባድ ዕቃ ማንሻ

(ክሬን) ተነሣ። ሮበርት እስከ ዛሬ በክብደት ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ወንድ ነው።

በሴቶች በኩል ደግሞ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ኔግሬስ ናት። 1888 ዓ.ም በባልቲሞር አውራጃ ሞታ ስትቀበር የነበራት ክብደት 425 ኪሎ ነበር።

በቀላልነት ደግሞ ወደር ያልተገኘለት ሆፕኪን ነው። ሆፕኪን በተወለደ በ17 ዓመት ስድስት ኪሎ ተኩል ብቻ ይመዝን ነበር።

## አወላለድ!

የሞስኮብ (የራሺያ) ሰዎች ወላዶች ናቸው። ከዳግማዊ አሌክሳንድር ዘንድ ቀርባ የተሸለመችው ወይዘሮ ቫሲሌት 69 ልጆች ወልዳለች። ቫሲሌት የሞተችው በ1872 ዓ.ም ነው። ቫሲሌት 69 ልጆች የወለደችው በ27 እርግዝና ነው። 16 ጊዜ መንታ ወልዳለች። ሰባት ጊዜ ሦስት ሦስት ልጆች ወልዳለች። አራት ጊዜ ደግሞ አራት አራት ልጆች ወለደች።

ቫሲሌት እስካሁን ድረስ በአወላለድ ታሪክ የበላይነቱን የያዘች ነች። ቫሲሌት ጨዋ ሴት በመሆንዋ ስልሳ ዘጠኙንም ልጆችዋን የወለደችው ካንዱ ከባልዋ ካቶ ፊደር ቫሲሌት ነው።

በደቡብ ቱርክ አዳና በተባለ ቀበሌ የምትኖር ፋጡማ የተባለች ሴት በ1961 ዓ.ም ሰኔ 3 ቀን የወለደችው ልጅ በተወለደ ዕለት 12 ኪሎ ይመዝን ነበር። እስካሁን የፋጡማን ልጅ ክብደት የደረሰ አልተወለደም።

በወንዶች በኩልም ብዙ ልጆች ያስወለዱ አሉ። እንዲያውም እስከ ምጽአት ድረስ ተወዳዳሪ ይገኝላቸዋል የማይባሉም አሉ። የፔርሺያ ሻህ የነበረው ፋቲ አሊ በ1882 ዓ.ም 154 ወንዶችና 560 ሴቶች በድምሩ 714 ልጆች ነበሩት።

በኮንጐ በኬኮቤና የቤኮቴ ነገዶች አለቃ የሆነው የሙሽንጊው ነዋሪ አቶ ሎኬንጉ አሁን በቅርቡ በ1969 ዓ.ም ከስምንት መቶ ሚስቶቹ የወለዳቸውን 750 ልጆቹን አስቆጥሯል። ይህ ሁሉ ቢሰበሰብ ሲንግን አይወዳደርም።

ማን ሲንግ ከ1592 ዓ.ም እስከ 1614 ዓ.ም በሕንድ አገር የጃይፑር ገዥ ነበር። አንድ ሺህ አምስት መቶ ሚስቶች ነበሩት። ከነዚሁ ሚሶቱች ያስወለዳቸው ልጆች አራት ሺህ ናቸው።

በሴቶች የአወላለድ ታሪክ ውስጥ ባንድ ጊዜ ብዙ ልጆች መውለድ አና ሮሚርን የሚስተካከላት የለም። አና ጀርመናዊት አንት። በ1600 ዓ.ም ጥር 9 ቀን ባንድ ጊዜ ሰባት ልጆች ወልዳለች። ከሰባቱ አስምቱ ሴቶች ሲሆኑ ሁለት ወንዶች ናቸው።

## የተጣበቁ ልጆች፤

በሲያም ውስጥ ባንጉሳኡ በተባለ አምባ በ1811 ዓ፣ም ሚያዝያ 15 ቀን የተጣበቁ መንታ ልጆች ተወልደዋል። ልጆቹ የተጣበቁት ከትከሻቸው ጀምረው ቍልቍል እስከ ዳሊያቸው ጐን ለጐን ነው።

ልጆቹ ተወልደው ማደግ እንደ ጀመሩ አንዱ ቻንግ ተባለ። ሁለተኛው ደግሞ ኢንግ ተባለ። እንደ ተጣበቁ አደጉ። በተወለዱ በ32 ዓመታቸው በ1843 ዓ.ም በሚያዝያ ወር እንደተጣበቁ ሁለቱም ሁለት ሚስቶች አገቡ። አንደኛይቱ ሴት ወይዘሮ ሣራ ስትባል ሌላይቱ ደግሞ ወይዘሮ አዴላይድ ትባለለች።

እነዚህ የተጣበቁ ሰዎች ከነዚሁ ሚስቶቻቸው 22 ልጆች አስወለዱ። አንደኛው አሥር ልጅ ሲአይስወለድ አንደኛው ተጣባቂ ደግሞ 12 ልጆች አስወለደ። እነዚህ ጉዶች በሕይወት የቆዩበት ዕድሜያቸው 62 ዓመት ነው። በ1874 ዓ.ም ጥር 17 ቀን አንደኛው ተጣባቂ ሞት። ያ ከሞተ ከሦስት ሰዓት በኋላ ሁለተኛው ተጣባቂ ወንድየው ሞተ።

## መንታ፤

መንታ መወለድ የተለመደ ነው። መንትዮቹ ሲወለዱ አንዱ ካንዱ በከብደት ይበልጣል። ግን በመንታ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ወይዘሮ ፊፌል ማይክሮፍት እኩል የሆኑ ልጅጆች ወልዳለች። በ1955 ዓ.ም በሚያዝያ ወር አሜሪካዊቷ የሚችጋን ነዋሪ የሆነችው ወይዘሮ ፌሬል በተወለደች በ፳፪

ዓመትዋ የወለደቻቸው መንታ ልጆች እያንዳንዳቸው በትክክል አምስት አምስት ኪሎ ይመዝኑ ነበር።

መንትዮች ብዙ ዕድሜ የላቸውም ይባላል፤ ግን ልክ አይደለም። በኖርዌይ ነሐሴ 2 ቀን ፲፱፻፳ ዓ.ም የአንድ መቶ አንድ ዓመት የልደት በዓላቸውን ያከበሩ መንትዮች ተገኝተዋል።

## ጥፍር

አንድ የቻይና ቄስ ጥፍሩን አሳድጎ ነበር። ቄሱ ጥፍሩን ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ ተንከባክቦ አሳደገው በመጨረሻው በ፲፱፻፲ ዓ.ም በሻንጋይ ከተማ ጥፍሩን አስለካ፤ የጥፍሩ እርዝመት ሁለት ክንድ ሆነ።

ጥፍር በቀን የአንድ ኢንች ሁለት መቶኛ ያድጋል። ከጥፍሮች ሁሉ የእጅ አውራ ጣት ጥፍሮች ቶሎ ያድጋሉ የእግር አውራ ጣት ጥፍር ደግሞ ቶሎ ታዳጊ አይደለም። ከአምስት እስከ ሰላሳ ዓእምት ዕድሜ ጥፍሮች ቶሎ ቶሎ ያድጋሉ። ከዚያ በኋላ ባለው ዕድሜ የጥፍሮች አስተዳደግ የደከመ ነው።

## ጢም

ሐንሰ ላኖሴት የተባለ የኖርዌጅያን ሰው ከ፲፰፻፸፪ ዓ.ም ጀምሮ ፴፮ ዓመታት ሙሉ ጢሙን አሳደገ። በ፲፱፻፲፪ ዓ.ም ጡሙ ቢለካ ፲፩ ጫማ ከስድስት ኢንች ሆነ። ሰባት ክንድ ያህል ማለት ነው።

## ሪዝ

በርዝማኔ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ሪዝ የማስሩሪያ ዲን ሪዝ ነው። ሕንዳዊው ማሱሪያ ዲን ዘጠኝ ዓመት ሪዙን አሳደገ። ለሪዙ መጠበቂያ በያመቱ ንሮ የኢትዮጵያ ብር ያህል ወጭ ያደርግ ነበር፥ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ጢሙ ቢለካ ፸፪ ኢንች ሆነ።

# ጠጉር

በሕድ ሀገር ሀኑማን በተባለ ገዳም የነበረ ያንድ መነኮሴ ጠጉር ርዝማኔ ሰባት ጫማ ከ፲ ኢንች ነበር። አምስት ክንድ ያህል ማለት ነው፤ መነኮሴው የሁለት ክንድ ቁመት ያለው አጭር ስለ ነበር ጠጉሩ በብዛት ከመሬት ይተኛ ነበር።

የጠጉር ቀለም ይለዋወጣል። ለምሳሌ ሰዎች ባረጁ ጊዜ ጠጉራቸው ቀለም ይነጣል። ይህ የሚሆነው ጠጉር ራሱን የሚያሳምርበት የራሱ ቀለም አለው። ፈረንጆች ፒግሜንት ይሉታል። ፒግሜንት የጠጉር አቅላሚ ቀለም ነው። ፒግሜንት የሚሠሩ ሴሎች አሉ። እነኚህ ሴሎች በእርጅና ወይም በበሽታ ሲደክሙ ወይም ሲጠፉ ፒግሜንት የተባለውን ቀለም የሚሠራው ስለሚጠፋ ጠጉር ቀለሙን ይለውጣል።

ጠጉር የሚመለጠ በሶስት ምክንያቶች ነው። ሕመም ጠጉርን ይመልጣል፤ ሁለተኛው ደግሞ ባርኔታ ማድረግ ነው። ራስ ላይ የሚያፍርፈው የባርኔጣ ክፈፍ ደም ወደ ጠጉር ወይም ወደ ራስ እንደ ልብ እንዳመላለስ ስለሚዘጋ ጠጉር ይመለጣል። ሦስተኛው በዘር ይወራረሳል። የጠጉር መመለጥ ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን ያጠቃል። በተለይም ብዙ ዘመን ባገለገሉ ወታደሮች ላይ ይታያል።

# ድምፅ፤

ካናሪ የተባለ የእስፓኝ ሰው ድምፁን ከስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ለማሰማት ችሏል፤ ካካናሪ በፊት አንድ ስሙ ያልተመዘገበ ሰው ድምፁን በጭለማ ጊዜ ከአሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር በላይ ለማሰማት ችሎ ነበር።

# እንቅልፍ፤

በ፲፱፻፶፱ ዓ፣ም በጥርና በየካቲት ወሮች የእንቅልፍ ውድድር ተደርጎ ዳዊት ኸንት የተባለ ሰው አሸንፏል። በውድድሩ የተወዳዳሪዎቹን መንቃት የሚቆጣጠር መሣሪያ ነበር። ዳዊት በተቆታጣሪው መሣሪያ እየተጠበቀ ሳይነቃ ፪፻፹፰ ሰዓቶች ተኝቷል ወይም አንቀላፍቷል። ዘጠኝ ለሊት ከዘጠኝ ሰዓት ማለት ነው።

## ጾም፤

በደቡብ አፍሪካ በጆሐንስበርግ ከተማ አጠገብ ኬኢው በተባለች ከተማ ወይዘሮ ካርኔልያ ፎስተር የተባለች ሴት ፩፻፪ ቀና ሙሉ ከውሃ በስተቀር ምንም ሳትቀምስ ጾማለች። ካርኔልያ ፩፻፪ ቀን ወይም ሦስት ወር ከ፲፪ ቀን የጾመችው በ፷፩ ዓመት ዕድሜዋ ነው።

## የረሀብ አድማ

እስከ ዛሬ ከተደረጉት የመራብ አድማዎች ወይም እህል አንበላም ብሎ የማደም ተግባር ተወዳዳሪ የሌለው በ፲፱፻፳ ዓ.ም በአይርላንድ የተደረገው የመራብ አዳም ነው። ኮርክ የተባለው ወህኒ ቤት ዘጠኝ ሰዎች ፍርድ ካልተስተካከለልን እህል አንቀምስም ብለው ፺፬ ቀናት ሙሉ የእህል ዘር ሳይቀምሱ ከርመዋል።

ከነዚሁ ከዘጠኙ ሰዎች መህል ዮሴፍ መርፊ የተባለ ሰው በሰባ ስድስተኛው ቀን ሞትዋል።

## መታፈን

ሳይተነፍሱ ብዙ መቆየት አይቻልም። ግን ሳይተነፍሱ በመቆየት የአሸናፊነቱን ደረጃ የያዘው ሮበርት ፎስተር ነው። የካሊፎርኒያው ነዋሪ አሜሪካዊው ሮበርት ፎስተር ፲፫ ደቂቃ ከአባ ሁለት ሴኮንድ በውሀ ውስጥ በመቆየቱ የመታፈን አሸናፊ ሆንዋል።

## እጅን እንደ እግር

ጆሐን ሁስሊንገር የተባለ ሰው በ1900 ዓ.ም በእጅ በመሔድ ተወዳዳሪ የሌለው አሸናፊ ሆኑዋል። ጆሐን በዚያ ዓ.ም ከቪየና ተነስቶ ፓሪስ ከተማ ድረስ እበጁ ተጉዟል። ከቪየና ፓሪስ ድረስ የተጓዘበት መንገድ ርቀት 871 ማይል ወይም 1393 ኪሎ ሜትር ነው። ይህን የእጅ ጉዞውን ለመጨስ የፈጀበት ጊዜ 55 ቀናት ከ10 ሰዓት ነው።

# ማልመድ

አራዊትን ለማዳ በማድረግ በኩል ካፒቴን አልፍሬድ ሰቼንደር በአውሬ አሰልጣኝነት የበላይነቱን ሥፍራ ይዟል። ካፒቴን አልፍሬድ በ1925 ዓ.ም ሰኔ 21 አንበሶችን ፍጹም ለማዳዎች አድርጓቸዋል።

# ጋብቻ

ወይዘሮ በቨርሊይ ኒና የተባለች የሎስ አንጀለስ ሴት በ1957 ዓ.ም በጥቅምት ወር በተወለደች 48 ዓመትዋ 14 ባሎች አግብታለች። ናኒ ባንድ ወር ውስጥ 14 ባሎች በሰማንያ እየተፈራረመች በማግባትዋ በሴቶች የጋብቻ ታሪክ ውስጥ የበላይነትን ሥፍራ ይዛለች። በዚያ ወር ውስጥ ከአሥራ አራቱም ባሎችዋ ጋር ሰማንያ (ውል) ነበራት።

ኒና 14 ባሎች ባንድ ወር ውስጥ ያገባችው ወንዶቹ እየተስማሙ ሳይሆን እያጭበረበረች ነው። የሚያገባት ሁሉ እሱ ብቻ ባል ሆኖ የሚፈርምላት እየመሰለው ነው። በኋላ ግን ባሎቹ ስለበዙና ኒናም አላደርስ ስላለች ተከሳለች።

በወንድ በኩል በሕንድ አገር የቪጃያና ጋር ንጉሥ ዳግማዊ ሐሪ ሐራ 12.000 ሚስቶች ነበሩት። ንጉሥ ሐሪ ሐራ በአሥራ ሁለት ሺህ ሚስቶቹ ላይ ተጨማሪ ላንዲት ሴት ብሎ ሲዋጋ በጦርነት ላይ ሞተ። ሐሪ ሐራ የተወለደው በ1398 ዓ.ም ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ246 ዓመተ ዓለም እስከ 210 ዓመተ ዓለም ቻይናን ይገዛ የነበረው ችን ሺ ሁአንግ ቲ 13.140 ሚስቶች ነበሩት። በወንዶች በኩል ቺን ሺን የሚወዳደር የለም።

በጋብቻ ታሪክ ውስጥ አብሮ በመኖር ከባልና ሚስቶች ሁሉ የበላይነቱን የያዙት ሩስያውያኖቹ (መስኰባውያኖቹ) አቶ ቴሙልጂና ወይዘሮ ናሪማን ናቸው። እነዚህ ሙሉ ሳይፋቱ ኖረው በ1853 ዓ.ም ነው። 87 ዓመታት ሙሉ ሳይፋቱ ኖረው በ1940 ዓ.ም የተፋቱት በሞት ነው። በ1940 ዓ.ም በነሐሴ ወር አቶ ቴሙልጅ ስለሞቱ ለመፋታት በቁ።

ፈረንጆች የየዓመቱን የጋብቻ በዓል እየሰየሙ ደልድለውታል። ባልና ሚስቶች ተጋብተው አንድ ዓመት ሲሞላቸው የሚያከብሩት የጋብቻ በዓል «የወረቀት» ይባላል።

2ኛው ዓመት የጥጥ፤

3ኛው ዓመት የቆዳ

4ኛው ዓመት የላይለን

5ኛው ዓመት የእንጨት

6ኛው ዓመት የብረት

7ኛው ዓመት የሱፍ ወይም የነሐስ

8ኛው ዓመት የመዳብ

9ኛው ዓመት የሸክላ

10ኛው ዓመት የቆርቆሮ

11ኛው ዓመት የጠንካራ ብረት

12ኛው ዓመት የሐር

13ኛው ዓመት የጠፍር ወይም የገመድ

14ኛው ዓመት የዝሆን ጥርስ

15ኛው ዓመት ክሪታይል

25ኛው ዓመት የብር

50ኛው ዓመት የወርቅ

60ኛው ዓመት የአልማዝ

# ሀብት

በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ የታወቁት ሀብታም የኩዌት ገዥ ልዑል ሻኪ - ሰር አብዱላህ አልሳሊም አልሰባህ ናቸው። ልዑሉ የተወለዱት በ1859 ዓ.ም ነው። ከልዑል በሳምንት 7.280.000 ያሜሪካ ብር ወይም 18 ሚሊዮን 200 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ገቢ አላቸው። የልዑሉ የዓመት ገቢ 378 ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ወይም 945 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው። ልዑሉ ይህን ሀብት የሚያገኙት ከዘይት (ከነዳጅ) ሽያጭ ነው።

ከተራ ሰዎች መሐል በሀብታምነቱ የታወቀው ወይም ተወዳዳሪ የሌለው ጄን - ፓውል ጌቲ ነው። ጄን ፓውል ጌቲ ዜግነቱ አሜሪካዊ ሲሆን ሀብታምነቱ በእንግሊዝ ሀገር ነው። ከዚያ ቀጥሎ ሮከፌለር ነው።

በውቅያኖሶች ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ ሀብት አለ። በውቅያኖሶች ውስጥ ያለው ወርቅ ወጥቶ ለዓለም ሕዝብ በሙሉ እኩል ቢከፈል ለያንዳንዱ ሰው ሃያ ኪሎ ወርቅና ሃያ ቶን ወይም ሃያ ሽህ 320 ኪሎ ብር ይደርሰዋል። በውቅያኖስ ውስጥ ያለውን ሀብት ለማውጣት ደግሞ ከሚወጣው ሀብት ሺህ ጊዜ የበለጠ ወጪ ይጠይቃል።

# ደሞዝ

የጀኔራል ሞተርስ ኩባይና የቦርዱ ሊቀ መንበር ፍሬ ደሪክ ጋሬት ደኔር በ1962 ዓ.ም ያገኘውን ደሞዝ የሚወዳደር የለም። በዚያ ዓመት ለፍሬደሪክ የተከፈለውን፤ 791457 ያሜሪካ ብር ወይም አንድ ሚሊዮን 978 ሺህ 687 የኢትዮጵያ ብር ነው።

ከፍተኛ ደሞዝ ያገኛል የሚባለው ያሜሪካ መንግሥት ፕሬዝዳንት ያመት ደመወዝ አንድ መቶ ሺ ያሜሪካ ብር ወይም 250 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ነው።

## ታይፒስት

በመኪና አጻጻፍ ማርግሬትን የሚወዳደራት አልተገኘም። አሜሪካዊቷ ማርግሬት በ1918 ዓ.ም ጥቅምት 21 ቀን በኒውዮርክ ከተማ ለውድድር ቀርባ በደቂቃ 170 ቃላት በመምታት አሸናፊ ሆናለች።

ታይፕ የተፈጠረው 1833 ዓ.ም ፖጊን በተባለ ፈረንሣዊ በማርሴል ከተማ ነው። ፖጊን የተፈጠረው የስሕፈት መኪና አስቸጋሪና ቅጥ የለሽ ስለ ነበረ በ1867 ዓ.ም በክርስቶፈር ላታም ሾሌ ተሻሽሎ ተፈጠረ።

## ሩጫ

ሳያርፍ ረጅም በመሮጥ ከዓለም ሩዋጮች የበላይነት ደረጃ ያያዘው ጂ ሳውንድርስ ነበር። ጂ ሳውንደርስ በ1882 ዓ.ም የካቲት 21 እና 22 ቀን በኒዮርክ ከተማ ያለማረፍ 127 ማይል ወይም 203 ኪሎ ሜትር ከ200 ሜትር ሮጥዋል። ይህን ርቀት የሮጠው በ22 ሰዓት ከ49 ደቂቃ ነው።

በ1953 ዓ.ም ግን ዋሊ ኤች ሐይዋርድ የተባለ ሰው ከሳውንደርስ የበላጭነቱን ሥፍራ ያዘ። ይህ የደቡብ አፍሪካ ሰው በእንግሊዝ ሀገር በ1953 ዓ.ም ኅዳር 20 ቀን በአምስት ሰዓት ሩቻውን ጀምሮ ኅዳር 21 በአምስት ሰዓት ሩጫውን ጨረሰ።

ሐይዋርድ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የሮጠው 159 ማይል ከ562 ያርድ ነው።

ከሐይዋርድ በፊት በ1929 ዓ.ም የአሜሪካ ሀገር የረጅም መንገድ ሩጫ ውድድር ተደርጐ ነበር፤ ውድድሩ የተደረገው ከኒውዮርክ እስከ ሎስ አንጀለስ ነበር። የመወዳደሪያው መንገድ ርዝመት 3610 ማይል ወይም 5776 አሜሪካዊ አሸናፊ ሆንዋል። ጆኒ ውድድሩ የፈጀበት ጊዜ 79 ቀናት ነው። ጆኒ በሰዓት የሮጠው መሐከለኛ ግምት 9686 ሜትር ነው።

# ማራቶን

የማራቶን ውድድር ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አበበ ቢቂላን የሚያህል ሰው ስልተገኘም። እያበበ ከፍተኛ አሸናፊነት ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ድል ማድረጉ ነው። በማራቶን ታሪክ ውስጥ ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ያሸነፈ እሩዋጭ ከአበበ በስተቀር የእልም።

ፊንላንድ የተባለችው ሀገር በመደጋገም ሁለት ጊዜ አሸንፋለች። ግን ተወዳዳሪው ወይም አሸናፊው እንደ አበባ ቢቂላ አንድ ሰው አልነበረም። ስለዚህ በማራቶን ታሪክ ውስጥ ባንድ ሰው አሸናፊነት ሁለት ጊዜ ድል ያገኘች ኢትዮጵያ ብቻ ናት።

የዓለም የማራቶን ሩጫ ውድድር የተጀመረው በ1896 ዓ.ም ነው። እስከ 1964 ዓ.ም የዓለም የማራቶን ውድድሮች ተደርገዋል። በነዚህ ውድድሮች ፈረንሣይ ሶስት ጊዜ ስታሸንፍ ሁለት ሁለት ጊዜ ያሸነፉ ኢትዮጵያውያን፤ አርጀንቲና፤ ፊንላድና አሜሪካ ናቸው።

የማራቶን ሩጫ ውድድር አኩሪያችን ስለሆነ የሀገራችን ሰዎች እስካሁን ያሉትን አሸናፊዎች እንዲያውቋቸው አስትሜአቸዋለሁ።

በ1896 ዓ.ም በግሪክ ዋና ከተማ አቴን ላይ በተደረገው ውድድር ኤስ ሉይስ የተባለ ግሪካዊ ውድድሩን በ2 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ከ20 ሴኮንድ ጨርሶ አሸነፈ።

በ1900 ዓ.ም በፈረንሣይ ዋና ከተማ ፓሪስ ላይ ሚችል ቲያቶ የተባለ ፈረንሣዊ በ2 ሰዓት ከ59 ሰዓት ከ28 ደቂቃ ከ53 ሴኮንድ ሮጦ አሸነፈ። አሁንም የግሪኩ ሪኮርድ አልተሰበረም።

በ1906 ዓ.ም አቴንስ ላይ በተደረገው ውድድር ደብልዩ ሼ ሸሪንግ የተባለ ካናዳዊ በ2 ሰዓት ከ51 ደቂቃ ከ23.3.5 ሴኮንድ በመሮጥ አሸነፈ። የግሪኩን ሯጭ ሬኮርድም ሰበረ።

በ1908 ዓ.ም በእግንሊዝ ሀገር ለንደን ከተማ ጆን ጄ ሐይስ የተባለ አሜሪካዊ በ2 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ከ18.4 ሴኮንድ በመሮጥ ሲያሸንፍ ሪኮርዱ በካናዳ እጅ ነበር።

በ1912 ዓ.ም በስዊድን አገር በስቶኮልም ከተማ በተደረገው ውድድር ኬ ኬ ማክ አርዘር የተባለ ደቡብ አፍሪካዊ በ2 ሰዓት ከ36 ደቂቃ ከ54.8 ሰከንድ አሸንፎ አዲስ ሬኮርድ ፈጠረ። አፍሪካም ለመጀመሪያ ጊዜ በማራቶን ሩጫ ድል አገኘች።

በ1916 ዓ.ም ውድድሩ አልተደረገም። በ1920 ዓ.ም ኤች ኮሌህማይኔን የተባለ የፊንላንድ ሰው በ2 ሰዓት ከ32 ደቂቃ ከ35. 4.5 ሰከንድ ሮጦ አሸነፈ። አዲስ ሬኮርድም ፈጠረ።

በ1924 ዓ.ም ፓሪስ ላይ ኤ ኦ ስቴንሮስ የተባለ የፊንላንድ ሰው በ2 ሰዓት 41 ደቂቃ ከ22. 6 ሴኮንድ ሮጦ አሸነፈ። የነበረውን ሬኮርድ ባይሰብርም ሬኮርዱ ያለው ያው በፊንላንድ እጅ ነው። አበበ ቢቂላ እስኪፈጠር ድረስ ፊንላድ ሁለቴ አከታትላ በጐልት ሯጮች ድል በማድረግዋ በማራቶን ታሪክ ትደነቅ ነበር።

በ1928 ዓ.ም አምስተርዳም ላይ በተደረገው ውድድር ኢል አኡፍል የተባላ ፈረንሣዊ አሸነፈ። የፈጀበት ጊዜ 2. ሰዓት ከ32 ደቂቃ ከ57 ሰከንድ ነበር። አሁንም ሪኮርዱ በፊንላንድ እጅ ነው።

በ1932 ዓ.ም ሎስ አንጀለስ ላይ ጁአን ዛቦላ የተባለ የአርጀንቲና ሰው 2. ሰዓት ተኩል 31 ደቂቃ ከ36 ሰከንድ በመሮት አሸንፈ። የፊንላንድ ሬኮርድም ተሰብረ።

በ1936 ዓ.ም በርሊን ላይ ኪቴይ ሶን የተባለ የጃፓን ሰው በ2 ሰዓት ከ29 ደቂቃ ከ19 ሰከንድ አሸንፎ አዲስ ሬኮርድ አመጣ። በመሐሉ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስለ ተነሳ ውድድሩ ተቋረ።

በ1948 ዓ.ም ለንደን ላይ በተደረገው ውድድር ዲ. ካብሬራ የተባለ የአርጀንቲና ሰው በ2 ሰዓት ከ34 ደቂቃ ከ15.6 ሰከንድ ሮጦ አሸንፈ። ሬኮርዱ (የበላይነቱ) ግን ከጃፓን እጅ አልወጣም።

በ1952 ዓ.ም ሒሊስንኪ ላይ ኢሚል ዛቶፒክ የተባለ የቸኮዝላቫኪያ ሰው በ2 ሰዓት ከ23 ደቂቃ ከ3.2 ሰከንድ በመሮጡ አሸንፈ። አዲስ ሬኮርድም ፈጠረ።

በ1956 ዓ.ም ሜልቡርን ላይ በተደረገው ውድድር አላኢን ሚሙን የተባለ የፈረንሣይ ሰው በ2 ሰዐት ከ25 ደቂቃ በመሮጥ ድል አደረገ፤ እንደገና አዲስ ሬኮርድ ፈጠረ።

በ1960 ዓ.ም በጃፓን ሀገር ቶኪዮ ከእትማ ላይ አሁንም ኢትዮጵያዊው አበበ ቢቂላ በ2 ሰዓት ከ12 ደቂቃ ከ11.2 ሰከንድ ሮጦ ማንም ያልሰበረውን የራሱን ሬኮርድ ራሱ ሰብሮ ድል አደረገ።

## ዳንስ

በየጊዜው የዳንስ ውድድሮች ተደርገዋል። ብዙውን ጊዜ ለዳንስ በሚደረገው ውድድር ከተወዳዳሪዎቹ የሚፈለገው በዳንስ ላይ የሚቆዩበት የጊዜ ብዛት ነው።

በዳንስ ታሪክ ውስጥ ከሰው ዘር እስካሁን ድረስ በደናሽነቱ የበላይነቱን የያዘው የአርጀንቲና ሰው ካርሎስ ሳንድርኒ ነው። በ1955 ዓ.ም በመስከረም ወር በቡኤኖስ አይረስ ከተማ በተደረገው የዳንስ ውድድር ካርሎስ ሳንድርኒ አሸናፊ ሁነዋል። ካርሎስ 106 ሰዓት ከ5 ደቂቃ አሥር ሰከንድ ያለማረፍ ደንሷል። ካርሎስ ያለማረፍ የደነሰው አራት ቀንና አራት ሌሊት ከአሥር ሰዓት በላይ መሆኑ ነው።

የካርሎስ አዳናሾች ሦስት ሴቶች ነበሩ። ሴቶቹ እየተፈራረቁ በማረፍ ተራ በተራ አዳንሰውታል፤ እስካሁን ከካርሎስ እኩል የደነሰ የለም።

## የከረቦ አመታት

ሳያቋርጡ ከረቦን በመምታት የዓለም ከረቦ በቺዎች የበላይ የሆነው ራየዲ ቫል የተባለ ሰው ነው። በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ ቦንት በተባለ ክለብ ጥቅምት 14 ቀን 1906 ዓ.ም የከረቦ ዓመታት ውድድሩን ጨረሰ። ራየዲ ቫል

ሳያቋርጥ ከረቦውን የመታበት ጊዜ መቶ ከአንድ ደቂቃ ከ15 ሴኮንድ ነው። ወይም በሌላው አነጋገር ሳያቋርጥ ከረቦውን የመታው አራት ቀንና አራት ሌሊት ካራት ሰዓት በላይ ማለት ነው።

## ፒያኖ

በፒያኖ አመታት የዓለም ፒያኖ ተጫዋቾች የበላይ ሔንዝ አርንፅ ነው። በ1955 ዓ.ም ግንቦት 1 ቀን በበርሊን ከተማ ሳያቋርጡ ፒያኖ የመምታት ውድድር ተደርጐ ሔንዝ አርንፅ የተባለ ጀርመን 423 ሰዓት ሳያቋርጥ በመምታቱ አሸናፊ ሆነዋል። ሔንዝ ሳያቋርጥ ወይም ሳያርፍ ፒያኖ የተጫወተባቸው 423 ሰዓታት ወደ ቀን ሲለወጡ 18 ቀንና 17 ሌሊት ከሶስት ሰዓት ናቸው።

ከሴት ፒያኖ ተጫዋቾች ደግሞ በእንግሊዝ አገር በኖርዘንበር ነዋሪ የሆነችው ወይዘሮ ሜሪ አሸንቶ በ1958 ዓ.ም በነሐሴ 18 ቀን እስከ ነሐሴ 23 ቀን ድረስ ሳታቋርጥ ወይም ሳታርፍ ፒያኖ ተጫውታ አሸንፋለች።

ወይዘሮ ሜሪ በአርባ ዓመት ዕድሜዋ ተወዳድራ አሸናፊ የሆነችው 133 ወይም ስድስት ቀንና አምስት ሌሊት ከአንድ ሰዓት ያለ ምንም ዕረፍት ተጫውታ ነው።

ፒያኖ የተፈጠረው በ1720 ዓ.ም ነው።

## ንግግር

በ1955 ዓ.ም የኢርላንድ ሰው የሆነው የቪንሸሀን በእንግሊዝ አገር ባደረገው ንግግር እስካሁን የሚወዳደረው አልተገኘም።

ከቪን ሸሀን ኅዳር 28 ቀን መናገር ጀምሮ ያለ ምንም ዕረፍት እየተናገረ ታኅሣሥ 3 ቀን ጨረሰ። ያለ ማቋረጥ የተናገረበት ጊዜ 133 ሰዓት ነው። ወይም ስድስት ቀንና አምስት ሌሊት ከአንድ ሰዓት ነው።

ከሴት ታናጋሪዎች እስካሁን የምትወዳደራት ያልተገኘለት የሰሜን ካርሊና ተወላጅ የሆነችው ወይዘሮ አልተን ክላን ናት። በ1958 ዓ.ም በነሐሴ ወር

በተደረገው የመናገር ውድድር የሴቶች አሸናፊ ሆናለች። ወይዘሮ አልተን ያለ ማቋረጥ የተናገረችበት ጊዜ 96 ሰዓት ከ54 ደቂቃ ከ11 ሰከንድ ነው። አራት ቀንና አራት ሌሊት ማለት ነው።

አመጋገብ

አይርላንዶች በድንች አበላል የላቸውም። እያንዳንዱ ሰው ባመት በመሐከለኛ ግምት 158 ኪሎ ድንች ይበላል።

የኰሎምቢያ ሰዎች ደግሞ ብዙ ስኳር ይፈጃሉ። በስኳር አመጋገብ በኩል የኰሎምቢያን ሰዎች የሚወዳደር የለም። አንድ ሰው ባመት በመካከለኛ ግምት 56 ኪሎ ስኳር ይመገባል።

በሥጋ አበላል የኡራጋይ ሰዎች አንደኞች ናቸው። አንድ ሰው በዓመት ይበላል ተብሎ የሚታሰብለት መሐከለኛ ድርሻ 120 ኪሎ ሥጋ ነው። እዚህ ላይ ከአንባቢዎች ጋር መግባባት ያስፈልጋል። አንድ ሰው በዓመት 120 ኪሎ ሥጋ ይበላል ሲባል በኛ ሀገር የበለጠ የሚባሉ እንዳሉ እናውቃለን። ያኛው ሒሳብ ግን በሰው ድርሻ ነው።

ለምሳሌ የኡራጋይ ሕዝብ ብዛት 2. ሚሊዮን 682 ሺህ ነው። የያንዳንዱ ሰው የዓመት የሥጋ ድርሻ 120 ኪሎ ሲሆን በዓመት ውስጥ የኡራጋይ 321 ሚሊዮን 840 ኪሎ ሥጋ ይበላል ማለት ነው። እንደ ገና ደምኅ ለምሳሌ በአሜሪካ ባመት ከዚህ የበለጠ ሥጋ ይበላል እንበል። ግን ያ በዓመት የተበላው ሥጋ ለያንዳንዱ ያሜሪካ ሕዝብ ሲተነተን የኡራጋይ የአንድ ሰው ድርሻ ያህል አይደርስም። ተግባባን? የድንቹም የስኳሩም አስተሳሰብ እንደዚሁ ነው።

## ትንባሆ

የደቡብ አሪካ ነጮች በትንባሆ አጫሽነት ከዓለም ሕዝቦች የበላይነቱን ይዘዋል። አንድ ሰው በዓመት 2.600 ሲጃራዎች ያጨሳል።

ሁለተኛነቱን ደረጃ የያዘው የአሜሪካ ሕዝብ ነው። በዓመት ሰባት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ሲጃራዎች ያጨሳሉ። ባሜሪካ ባመት የሚጨሱት

ሲጃራዎች 503 ሺህ ሚሊዮን ናቸው። አንድ ሰው ባመት 2580 ሲጃራዎች ያጨሳል። አስተሳሰቡ ቅድም እንደ ተናገነጋገርበት እንደ ሥጋው ሒሳብ ነው።

ውድ ትንባሆ ፓርታጋስ የተባለ ሲጋር ነው። በአሜሪካ ውስጥ በሰባት ዶላር ተኩል ይሸጣል።

ከሲጃራ ደምነ ውድ የሆነው ሮያል ድራጌንስ የተባለው ነው። ሲጃራው የሚሠራው በምድረ ግብፅ በፖርት ሳይድ ነው። ይህ ሲጃራ በኤሮፕ ውስጥ አንዱ ፓኬ (አስሩ ሲጃራ) ሶስት የኢትዮጵያ ብር ሒሳብ ይሸጣል።

በዓለም ካሉ ሲጃራዎች ሁሉ በብዛት የሚሸጥ ስጃራ ካሜል ነው። ባመት 65 ሚሊያርድ ሁለት መቶ ሚሊዮን ፓኬ ይሸጣል።

በዓለም ካሉት የሲጃራ ፋብሪካዎች ሁሉ ትልቁ ሬይኖልድስ ትንባሆ ካንፓኒ ነው። ዊኒስተንና ሳሊም ሲጃራዎች የሚሠሩበት ነው። ኩባንያው በ1961 ዓ.ም መጨረሻ በወጣው መግለጫ በዚያ ዓመት 859 ሚሊዮን 229 ሺህ ዶላር (ማሬሪካ ብር) ማግኘቱን ገልጿል።

# ዓለም

## መሬት

የመሬት ክብደት 6.588.000.000.000.000.000.000. ቶን ነው። የመሬት ዕድሜ በ1962 ዓ.ም በሰኔ ወር ከሳይንቲስቶች የወጥው መግለጫ እንዳስረዳው አምስት ሺህ ሚሊዮን ዓመታት እንደ ሆናት ተናግሯል። የሶቪዬት ሳይንቲስቶ ደግሞ ከዚያ ወዲህ 6.500 ሚሊዮን ዓመታት ዕድሜ ያለውን ድንጋይ (ቋጥኝ) ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

## ውቅያኖስ

መሬት ካላት ክብደት ውስጥ ሩቡን እጅ የያዙት ውቅያኖሶች ናቸው። የቅያኖሶች ክብደት 1.580. 000.000.000.000.000.000. ቶን ነው።

ከውቅያኖሶች ሁሉ ትልቁ ፓስፊክ ውቅያኖስ ነው። ፓስፊክ ውቅያኖስ 63 ሚሊዮን 801 ሺህ 668 ስኩየር ማይል ስፋት አለው። የመስኰብ መርማሪዎች በ1959 ዓ.ም በመጋቢት ወር ፓሲፊክ ውቅያኖስ 36198 ጫማዎች ጥልቀት እንዳለው ተናግረዋል። ያም ቢሆን የፓስፊክ ጥልቀት መሐከለኛው ወይም ፈረንጆች እንደሚሉት አቬሬጁ 14.048 ጫማ ነው።

አትላንቲክ ውቅያኖስ 28 ሚሊዮን 356 ሺህ 276 እስኩየር ማይል ስፋት ሲኖረው የጥልቀቱ መሐከለኛ ውጤት 13 ሺህ ሁለት ጫማዎች ነው።

አርክቲክ ውቅያኖስ አምስት ሚሊዮን 440 ሺህ 197 እስኩየር ማይል ስፋት ሲኖረው የጥልቀቱ መሐከለኛ ውጤት ሦስት ሺህ 953 ጫማዎች ነው።

ከውቅያኖስ ሌላ በዓለም የታወቁት ታላላቅ ባሕሮች 21 ናቸው። እነዚህ ባሕሮች ከ25 ሺህ እስኩየር ማይል በላይ ስፋት ያላቸው ናቸው። መዘርዘሩ አንባቢን ማድከም ስለመሰለኝ ትቼዋለሁ።

## ከዋክብት

በሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብት ስንት እንደ ሆኑ የሚያውቅ ሊቅ እስካሁን አልተገኘም። ሊቃውንቶቹ እስካሁን መርምረ እንዳገኙት ጥሩ ዓይን ያለው ሰው በጠራ ሰማይ ውስጥ ያለ ቴሌስኰፕ ዘጠኝ ሺህ ከዋክብት ሊመለከት ይቻላል። ይህም ቢሆን ሰውዬው ሙሉን ሰማይ ለማየት ስለማይችል ከዋክብትን በሙሉ አየ ሊባል አይቻልም። አንዳንዴም አራት ሺህ ከዋክብት ብቻ ይመለከታል። የከዋክብት ቀለም በያይነቱ ነው። ነጭ፤ ብጫ፤ ሰማያዊ፤ ሮዝ፤ አረንጓዴም ቀለም ያላባቸው አሉ፤ የወተት መንገድ በተባሉት የከዋክብት ትይንት ቢያንስ 100 ሺህ ሚሊዮን ከዋክብት እንዳሉ ሊቃውንት ይገምታሉ። ከእርቀታቸው የተነሳ ባንድነት የፈሰሱ ይምሰሉ እንጂ የከዋክብት አኗኗር አንዱ ካንዱ በጣም የተራራቀ ነው። መጠናቸውም እኛ እንደምንመለከታቸው ሳይሆን በጣም ግዙፍ ናቸው።

# ፀሐይ

ፀሐይ ብርሃን መስጠት የጀመረችው መቼ እንደሆነ የሚያውቅ አንድም የለ። ብዙዎቹ እንዲሁ በደፈናው ፀሐይ ለብዙ ዘመናት ሙቀትና ብርሃን ስትሰጥ ኑራለች ይላሉ። ፀሐይ ከተፈጠረች ጀምሮ እስካሁን ድረስ የብርሃንና የሙቀት መጠን ተግባርዋን አንዴም ሳታቋርጥ ኖራለች።

በፀሐይና በመሬት መሐል ያለው መራራቅ ቋሚ አይደለም። መሬት ዓመት ሙሉ ፀሐይን ስትዞር በመኖርዋ መሬት አንዴ ለፀሐይ ስትቀርብ አንዴ ደግሞ ትርቃታለች። በመሬትና በፀሐይ መካከል ያለ ርቀት በታህሣሥ ወር 91 ሚሊዮን 500 ሺህ ማይል ይሆናል። በሐምሌ ወር ደግሞ 94 ሚሊዮን 500 ሺህ ማይል ይራራቃሉ። በዚህም ምክንያት ክረምትና በጋ ይፈራረቃሉ።

ፀሐይ ላይ ያለው ግለት 11 ሺህ ዲግሪ ፋራናይት እንደሚሆን ይገመልታል። ከፀሐይ እምበር (ከመሐልዋ) ላይ ያለው የሙቀት ልክ ግን 40 ሚሊዮን ዲግሪ እንደሚያደርስ ሊቃውንት ገምተውታል። ይህ ፀሐይ ላይ ያለ ነበልባል ከፀሐይና ከመሬት መሐል ያለው 93 ሚሊዮን ማይል መሐከለኛ ርቀት አቋርጦ በስምንት ደቂቃ ውስጥ ከመሬት ይደርሳል። ሊቃውንቶች እንደሚሉት የፀሐይ ብርሃን ፍጥነት ባንድ ሴኮንድ 186.270 ማይል ይጓዛል።

# ወንዝ

ከወንዞች ሁሉ ረጅሙ ዓባይ ነው። አባይ 4.145 ማይል ይጓዛል። የዓባይ ርዝመት የሚለካው ከነጭ ዓባይ አንስቶ ሜዲትራኒያን ባሕር እስኪገባ ድረስ ነው።

ሁለተኛው ረጅሙ ወንዝ አማዞን ነው። አማዞን 3.912 ማይል ይጓዛል። ሦስተኛው ረጅም ወንዝ ደግሞ ሚሲሲፒ ነው።

በፈሳሽነት ከሁሉ ብልጫ ያለው አማዞን ነው። የአማዞን ወንዝ በሰከንድ 3.5 ሚሊዮን ኩቢክ ጫማ ውሀ ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ ያፈሳል ፡

## ፏፏቴ

ከፏፏቴዎች ሁሉ ብልጫ ያለው ቬኑዙኤላ የሚገኘው አንግል የተባለው ፏፏቴ ውሀ ነው። 3.212 ጫማዎች ይወረወራል። ከአንልግ ቀትሎ ሁለተኛነቱን የሚይዘው በአፍሪካ ውስጥ በደቡብ አፍሪካ የሚገኘው ናታል የተባለው ነው። ናታል 3110 ጫማዎች ይወረወራርሉ።

## ሐይቅ

በጥልቀቱ በዓለም ትልቁ ሐይቅ የሚገኘው በሶቪየት ግዛት በሲቤሪያ ነው። ባይካል ይሉታል። እብይካል 385 ቪች የተባለ ሰው በ1957 ዓ.ም የዚህን ሐይቅ ጥልቀት 4364 ለከቶች ጫማዎች ሆነዋል።

## የተከፋፈሉ ዓለማት፤

እስያ ሰፊ እህገር ነው፤ ከሁሉም ብልጫ አለው። የእስያ ስፋት 16 ሚሊዮን 900 ሺህ እስኩየር ማይል ነው። እስያ ከሰሜን ወደ ደቡብ 5.300 ማይል ርዝመት ሲኖረው ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ ስድስት ሺህ ማይል ርዝመት አለው።

ቀጥሎ አፍሪካ ነው። አፍሪካ 11 ሚሊዮን 500 እስኩየር ማይል ስፋት አለው። የአፍሪካ ከሰሜን ወደ ደቡብ ርዝመቱ አምስት ሺህ ማይልስ ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ 4. 700 ማይል ነው።

ቀጥሎ ሰሜናዊ አሜሪካ ነው። ዘጠኝ ሚሊዮን 300 ሺህ እስኩየር ማይል ስፋት አለው።

ይህ አለካከ ደሴቶቹን ጨምሮ ነው። ሰሜን አሜሪካ ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ርዝመት 5.300 ማይል ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ርዝማኔ ደግሞ አራት ሺህ ማይል ነው።

ደቡብ አሜሪካ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ እስኩየር ማይል ስፋት አለው። ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ርዝመት 4.750 ማይል ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ርዝማት ደግሞ 3.100 ማይል ነው።

ኤሮፕ ሶስት ሚሊዮን 750 እስኩየር ማይል ስፋት አለው። ኤሮፕ ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ርዝመት 2.400 ማይል ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ርዝመት ደግሞ 3.100 ማይል ነው።

ኤሮፕ ሶስት ሚሊዮን 700 ሺህ እስኩየር ማይል ስፋት አለው። ኤሮፕ ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ርዝማኔ 2.400 ማይል ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ርቀት ደግሞ 3.800 ማይል ነው።

አውስትራሊያ ሁለት ሚሊዮን 950 ሺህ እስኩየር ማይል ስፋት አለው። አውስትራሊያ ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ርዝመት 1970 ማይል ሲሆን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ርቀት 2.400 ማይል ነው።

አንታርቲካ 5 ሚሊዮን 300 ሺህ እስኩየር ማይል ስፋት አለው።

## የመሬት መንቀጥቀጥ፤

በ1923 ዓ.ም ታህሣሥ 1 ቀን ከቀን በ5 ሰዓት ከ58 ደቂቃ ላይ በጃፓን አገር ክዋንቶ በተባለው አውራጃ የደረሰውን የመሬት መንቀጥቀጥ የሚያህል እስከ ዛሬ በምድር ላይ አልደረሰም።

በዚያ ክዋንቶ አውራጃ በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥ 142.807 ሰዎች ሞተዋል። የመሬት መንቀጥቀጡ በንብረት ላይ ያደረሰው ጉዳት ሰባት ሚሊያርድ የኢትዮጵያ ብር ነው። በዓለም ከደረሱት የመሬት መንቀጥቀጦች ሁሉ ትልቅ ግዳት ያደረሰው ይሔ ነው።

## ግዛት

በዓለም ካሉ መንግሥታቶች ሁሉ የተባበረው የሶቪዬ ሬፐብሊል (መስኮብ) ሰፊ ግዛት አለው።

የግዛቱ ጠቅላላ ስፋት ስምንት ሚሊዮን 649.550 እስኩየር ማይልስ ነው። ከጠቅላላው የምድር ስፋት ከመቶው አሥራ አምስቱን እጅ ይዟል።

የተባበረው የሶቪየት ሬፑብሊክ ግዛት ከምሥራቅ ጠረፉ እስከ ምዕራብ ጠረፉ ድረስ ያለው ርዝመት 5.580 ማይል ሲሆን ከሰሜን ጠረፉ እስከ ደቡብ ወሰኑ ድረስ ያለው ርቀት 2790 ማይል ነው።

ትንሺቱ የግዛት ሀገር ቫቲካን ናት። የቫቲካን ጠቅላላ ስፋት 108.7 ኤክርስ ነው።

## ሕዝብ

አሁን በዓለም ላይ ያለው ሕዝብ ብዛት 3220 ሚሊዮን ነው። ሁለት ሺህ ዓ.ም ላይ የዓለም ሕዝብ ብዛት 6.605 ሚሊዮን እንደሚያደርስ ይገመታል።

ባለፉት 600 ሺህ ዓመታት ውስጥ 76 ሚሊያርድ ሰዎች ተወልደው እንደ ሞቱ ሊቃውንቶች ይናገራሉ። ባሁኑ ዘመን በመላው ዓለም በያንዳንዱ ሰዓት ውስጥ 13 500 ልጆች ሲወለዱ 6.500 ሰዎች ይሞታሉ ይባላል።

በዛሬው ዓለም ብዙ ሕዝብ ያለው መንግሥት ቻይና ነው። በ1963 ዓ.ም በተደረገው ቆጠራ 740 ሚሊዮን ሕዝብ እንዳለበት ታውቋል። በዚህ ብዛት ቻይናዎች ከጠቅላላው የዓለም ሕዝብ ከመቶው እጅ ሃያ ሶስቱን ይዘዋል።

ጥቂት ሕዝብ ካላቸው መንግሥታት የመጨረሻይቱ ቫቲካን ናት። የቫቲካን ሕዝብ 970 ብቻ ነው።

የየአህጉሩን ሕዝብ የተነተንረው እንደ ሆነ እንዲህ ይሆናል። በእስያ 1.783 ሚሊዮን ሕዝቦች አሉ። በኤሮፕ 440 ሚሊዮን፤ በአፍሪካ 304 ሚሊዮን በሰሜን አሜሪካ 286 ሚሊዮን በደቡብ አሜሪካ 162 ሚሊዮን ሕዝብ አለ። በየቁርጥራጩ ሀገር የተበታተኑም አሉ።

## ግራኝ

ዛሬ በዓለም ላይ 200 ሚሊዮን ግራኞች ወይም በግራ እጃቸው የሚሠሩ ሰዎች አሉ።

# ሃይማኖት

በዓለም ካሉት ሃይማኖቶች ሁሉ እንደ ክርስቲያን ሃይማንቶ ብዙ ተከታይ ያለው የለም። ዛሬ በመላው ዓለም ላይ 950 ሚሊዮን 550 ሺህ ክርስቲያኖች አሉ። በተከታይ ብዛት የእስልምና ሃይማኖት ሁለተኛነትን ይይዛል። እብዛሬው ዓለም 455 ሚሊዮን 785 ሺህ እስላሞች አሉ ፡

እንደምናውቀው የክርስቲያን ሃይማኖት ግንዱ አንድ ቢሆንም በሶስት ዋና ዋና ዘርፍ የተከፈለ ነው።

ካቶሊክ፤ ፕሮቴስታንትና አርቶዶክስ ናቸው። ባካቶሊክ እምነት ውስጥ 584 ሚሊዮን 493 ሺህ፤ በፕሮቴስታንት እምነት ውስጥ 224 ሚሊዮን 65 ሺህ ተከታዮች አሉ፤ በኦርቶዶክስ እምነት ውስጥ 142 ሚሊዮን 55 ሺህ ተከታዮች አሉ።

በዓለም የታወቁት ትልልቅ ሃይማኖት አሥር ናቸው። ከአሥሩ ስለ ሁለቱ ተነጋግረናል። የተቀሩት እነኝህ ናቸው።

ይሁዲ 13 ሚሊዮን 211 ሺህ ተከታዮች፤

ዞሪስቲሪያን 145 ሺህ ተከታዮች፤

ሺንቶ 67 ሚሊየን 155 ሺህ ተከታዮች፤

ቶይስት 51 ሚሊዮን 305 ሺህ ተከታዮች፤

ኮኖፌሽያን 350 ሚሊዮን 850 ሺህ ተከታዮች፤

ቡዲስት 161 ሚሊዮን 850 ሺህ ተከታዮች፤

ሒንዱ 395 ሚሊዮን 191 ሺህ ተከታዮች አሏቸው።

# ቋንቋ

ክርስቶስ ያስተምርበት የነበረው ቋንቋ አራማይክ ይባላል። የክርስቶስ ተከታዮችም ሐዋርያቶች ያስተማሩት በዚሁ አራማያክ በተባለ ቋንቋ ነው። አራማይክ በዚያ ዘመን የሲሪያና የፓሌስታይን ሕዝቦች መናገሪያ ነበር፤

የአራማይክ ቋንቋ ሊጠፋ የቻለው በእስልምና ሃይማኖት በተስፋፋበት ዘመን አረብኛ ስለተደረበበት ነው። ዛሬ በደማስቆ አጠገብ የሚገኙ ሶስት መንደሮች ብቻ በአራማይክ ቋንቋ ይጠቀማሉ። እነዚህ ሕዝቦች በዚህ ቋንቋ በመነጋገራቸው በጣም ይኮሩበታል።

በፈረንሣይ ሀገር ደግሞ አዚሊአን የተባለ ቋንቋ አለ። ይህ ቋንቋ ከክርስቶስ በፊት 15.000 ዓመታት እንዳለው ይነገራል። የሰማርያ ቋንቋ ደግሞ ከክርስቶስ በፊት 3.500 ዓመታት ዕድሜ አለው፡

ብዙ ሕዝብ የሚናገረው ቋንቋ ማንዳሪን የተባለው የቻይና ቋንቋ ነው። ማንዳሪን በተባለው ቋንቋ 493 ሚሊዮን ሕዝቦች ይነጋገሩበታል። ከዚያ ቀጥሎ ሁለተኛነቱን የሚይዘው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ብቻት 291 ሚሊየን ነው።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ 800 ሺህ ቃላት አሉበት። በቃላት ብዛት ከሌሎቹ ቋንቋዎች ሁሉ እንግሊዝኛ ይበልጣል። ዛሬ በዓለም ላይ ያሉት ቋንቋዎች ሶስት ሺህ ናቸው። እነዚህ ሶስት ሺህ ቋንቋዎች ብዙ ሕዝብ የሚነጋገርባቸው ናቸው። ጥቂት ሕዝብ የሚነጋገርባቸው የነገድ ቋንቋዎች ከቁጥር አልገቡም።

## ፊደላት

የሴሜቲክ ፊደል ከክርስቶስ በፊት ሁለት ሺህ ዓመታት ዕድሜ አለው። በዓለም ካሉት ፊደላት ሁሉ ብዙ ፊደል ያለው አማርኛ ነው። 300 ያህል ፊደላት አሉበት። በፊደላት ብዛት ከዓለም አንደኞች ነን።

ጥቂት ፊደል ያላቸው ሐዋውያን ናቸው። ጠቅላላ የፊደላቸው ብዛት 12 ነው።

## ቁጥር

ከቁጥሮቹ ሁሉ ብዙ ወይም ትልቁ ሴንትሊዮን ነው። አንድ ሴንቲሊዮን ለመጻፍ 1 ጽፎ 600 ዜሮዎች ማስከተል ነው። ሴንቲሊዮን የሚያገለግለው ለሳይንቲስቶች ብቻ ነው። ሌላው ምኑን ይቆጥረዋል?

በነገዶች መሐል ካሉ አቆጣጠሮች ጥቂት የሚቆጥሩ ያንኮሰ ውስጥ የሚገኙ ያማዞን ጐሣዎች ናቸው። ቁጥራቸው ፔትራ፤ ሮሪን፤ ኩአሮአክ ይባላል፡ በኛ ሲተረጐም አንድ ሁለት ሦስት ማለት ነው። ከዚህ በላይ መቁጠር አይችሉም። ማላይ ውስጥ ያሉ ቲማኣር የተባሉ ጐሣዎችም አቆጣጠራቸው ከሶት አያልፍም።

## ዓይን

አዝማሪዎቻችን «ዓይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው» ብለዋል። ሊሆንም ላይሆን ይችላል። ዓይን ማያ መሆኑ እናውቃለን። ማየት የሚችለው በማንጸባረቅ (ሬፍሌክት) ነው። በዚህ ምክንያት አይን ያለ ብርሃን ለማየት አይችልም።

በሁለትና በአንድ ዓይን መካከል ብዙ ልዩነት አለ። አንድ ዓይና አስተካክሎ የማያየውን ባለ ሁለት ዓይን በሚገባ ያየዋል። ስለ ዓይን ብዙ ታሪክ ይተረካል። የኔይቱ መጽሐፍ ግን ዓላማዋ በሚገባ ተንትና መተረክ ሳይሆን ባጭሩ ብዙ እውቀትን ለመግለጽ ስለ ሆነ ታሪክ አታበዛም።

ሽፋል የተሠራው ለጌጥ ሳይሆን ለዓይን ጋሻ ዣግሬነት ነው። ሽፋል ባይኖር ኖሮ ባላበን ቁጥር ከግንባራችን ላይ የወረደው ላብ ከዓይናችን ይገባ ነበር። ይህ እንዳይሆን እግዚአብሔር ለላብ ለገጅያ ሽፋልን ፈጠረ።

የዓይን የማይት ዓቅሙ የተወሰነ ነው። ለጥ ባለ ሜዳ ወይም ከትልቅ ባሕር ዳር ብንቆም ዓይን የማየት ችሎታው እምን ድረስ እንደ ሆነ ለማወቅ እንችላለን። የዓይን የማየት ችሎታው ሲያቆም ባሕሩና ሰማዩ የተሳሳሙ (የተገናኙ) ይመስሉናል። አድማስ እንለዋለን።

አንድ ልጅ ከትልቅ ባሕር ዳር ቆሞ ወደ ፊት ቢያይ የሚያየው ርቀት 2 ማይል ተኩል ነው። ልጁ ከባሕር በላይ መቶ ጫማዎች ከፍታ ካለው ሥፍራ ቆሞ ቢመለከት 13 ማይል ከሩብ ርቀት ድረስ ሊያይ ይችላል። ይህ የሚሆነው በፊት ለፊቱ የማየቱን ኃይል የሚያግደው ዛፍ ወይም ተራራ ያለበለዚያ ሕንፃዎች የሌሉ እንደ ሆነ ነው።

ከባሕር በላይ አንድ ጫማ ባለው ከፍታ ላይ ብንሆን የምናየው ርቀት አንድ ማይል ከሩብ ነው። አምስት ጫማ ከፍታ ባለው ቦታ ላይ ብንቆም ደግሞ ሶስት ማይል ርቀት እናያለን። እንግዲህ እያለ የማየት ችሎታ እንደ ቦታው ከፍተኛነት ይለዋወጣል።

ይህን በጠራ ሥፍራ ያለውን የማየት ችሎታ ሊቃውንት አንድ ጫማ ከፍታ ጀምረው በየተራው ተንትነውታል። ለምሳሌ 5.280 ጫማ ከባሕር በላይ ከፍታ ባለው ሥፍራ ሆነን አውላላውን ሜዳ ወይም ውቅያኖስን ብንመለከት 96 ማይል ድረስ ማየት እንችላለን።

## ጦርነት

እስካሁን ከተደረጉት ጦርነቶች ሁሉ ረጅም ጊዜ የወሰደው በፈረንሣይና በእንግሊዝ መሐል የተደረገረው ጦርነት ነው። ጦርነቱ በ1338 ዓ.ም ተጀምሮ በመቶ አሥራ አምስት ዓመቱ 1453 ዓ.ም ተፈጸመ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተፈጸሙ ጦርነቶች መሐል እንግሊዝና ዛንዚባር ያደረጉት ውጊያ ነው። ጦርነቱ በ1896 ዓ.ም ነሐሴ 27 ዓም ከጧቱ ሶስት ሰዓት ከሁለት ደቂቃ ስሆን ተጀምሮ በተጀመረ በ38 ደቂቃ ውስጥ ሦስት ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ላይ ተፈጸመ።

ብዙ ደም የፈሰሰበትና ብዙ ወጪ የተደረገበት ጦርነት 2ኛው የዓለም ጦርነት ነው። በ2ኛው ጦረንት 22 ሚሊዮን 60 ሺህ ሰዎች ሞተዋል። በዚሁ ጦርነት የቆሰሉት ሰዎች ብዛት ደግሞ 34 ሚሊዮን 300 ሺህ ነው። በጠቅላላው በ2ኛው የዓለም ጦርነት የ56 ሚሊዮን 360 ሺህ ሰዎች ደም ፈሷል።

2ኛው የዓለም ጦርነት ብዙ ደም የፈሰሰበት ብቻ ሳይሆን ጊዜ ሀብት ወጪ የተደረገበትም ነው። በ1959 ዓ.ም በግንቦት ወር የሶቪየት ሕብረት ሊቃውንት በሰጡት ጋዜጣዊ ማረጋገጫ መሠረት በ2ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ለጦርነት ወጪ የተደረገው ገንዘብ 2.500 ሚሊያርድ ሩብ ወይም 280 ሺህ ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ያለበለዚያም 700 ሺህ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው።

# ወህኒ ቤት

በዓለም ካሉ ወህኒ ቤቶች ሁሉ ትልቁ በሶቪየት ኅብረት ግዛት ውስጥ ይገኛል። ወህኒ ቤቱ 40 ሺህ ሰዎች ለመያዝ ይችላል።

ትንሺቱ ወህኒ ቤት የምትገኘው አስሎ ከተማ ነው። ወህኒ ቤትዋ የምትይዘው ሁለት ሰዎች ብቻ ነው።

# ንግድ፤

## ኩባንያ

ዛሬ በዓለም ካሉት ኩባንያዎች ሁሉ አሮጌው ወይም ጥንታዊ ኩባንያ የሚገኘው በስዊድን ሀገር ነው። ኩባንያው የሚገኘው በስዊድን ሀገር ነው። ኩባንያው ያውስቶራ ኮፖበርግስ በርግስላግስ ይባላል። ይህ ኩባንያ የተቋቋመው በ1288 ዓ.ም ሰኔ 16 ቀን ነው።

ከነጋድ ኩባንያዎች ሁሉ ከፍተኛ ገቢ ያለው የአሜሪካ የቴሌፎን የቴሌግራፍ ኩባንያ ነው። 1963 ዓ.ም ጥር 1 ቀን ኩባንያው ባወጣው መግለጫ ባለፈው ዓእምት 26 ሚሊያርድ 716 ሚሊዮን 536 ሺህ ዶላር ወይም 66 ሚሊያርድ 791 ሚሊያርድ 340 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ገቢ አግኝቷል።

ኩባንያው በዚያ ዓመት ሠርቶ ያወጣቸው ስልኮች፤ 56 ሚሊዮን 986.313 ናቸው። ኩባንያው 728.978 ሠራተኞች አሉት። የኩባንያውን መቋቋሚያ ገንዘብ ያዋጡት (ሼር ሆል ደርስ) 2 ሚሊዮን 210.671 ናቸው። በ1961 ዓ.ም በሚያዝያ ወር በተደረገው የአባሎች ጉባኤ ሃያ ሺህ አባልቾ ተሰብስበው ነበር። ይህ ጉባኤ ራሱ እስከ ዛሬ በጉባኤተኞች ብዛት በዓለም ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነው።

# ትርፍ

እስከ ዛሬ ካሉ ነጋዴዎች ሁሉ ትርፍ በማትረፍ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ጄኔራል ሞተርስ ኮርፐሬሽን እን። በ1962 ዓ.ም ባንድ ዓመት ያገኘው ትርፍ አንድ ሚሊዮን ሚሊያርድ 459 ሚሊዮን 77.450 ዶላር ወይም ሶስት ሚሊያርድ 647 ሚሊዮን 693.625 የኢትዮጵያ ብር ነው።

# ኪሣራ

ጄኔራል ዲናሚክስ ኰርፐሬሽን የተባለው የአኤሮፐላን ፋብሪካ በአከሣሥር ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነው። 1961 ዓ.ም 470 ሚሊዮን ዶላር ወይም አንድ ሚሊያርድ 175 ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር ከስሯል።

ፋብሪካ

በዓለም ካሉት ፋብሪካዎች ሁሉ ትልቁ ጄኔራል ሞተር ኮፐሬሽን ነው።

# ሆቴል

በዓለም የታወቀው የሒልተን የሆቴል ኩባንያ ነው። ሒልተን በ17 አገሮች ላይ ሃምሳ አራት ሆቴል ቤቶች አሉት። በነዚህ ሆቴል ቤቶች 31.221 ክፍሎችና ሰላሳ ሺህ ሠራተኞች አሉ። የሒልተን ኩባንያ ባመት 300 ሚሊዮን ዶላር ወይም 750 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ገቢ አለው።

የሒልተን ኩባንያ ካሉት ሆቴል ቤቶች ሁሉ በቺጋጐ ከተማ ያእልው ኮንራድ ሒልተን የተባለው ሆቴል ቤቱ ይበልጣል። የሆቴል ቤቱ ሕንፃ 25 ፎቆች አሉት። በነዚህ ሃያ አምስት ፎቆች ውስጥ 3.000 የእንግዶች ማረፊያ መኝታ ቤቶች አሉ። (አንድ እንግዳ በያንዳንዱ መኝታ ቤት አንዳንድ ቀን ብቻ እያደረ የመኝታ ክፍሎችን ሁሉ ለማዳረስ ቢፈልግ ሰባት ዓመት ይፈጅበታል። )

በዚያ ሆቴል ቤት ሁለት ሺህ ሠራተኞች አሉ። ከነዚሁ ሰባዋኦቹ የስልክ ኦፕሬተሮች ናቸው። ሰባ ሁለት የአሳንሰር (ሊፍት) አመላላሾች አሉ። የሆቴል ቤቱ ልብስ አጣቢዎች ሁለት መቶ ናቸው።

የሒልተን ኩባንያ በድርጅቱ ከፍተኛነት በብዛቱ ተወዳዳሪ አይኑረው እንጂ በገበያና በሕንፃ ትልቅነት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው በኒውዮርክ ከተማ ያእልው ዎልደርፍ አስቶሪያ የተባለው ሆቴል ነው።

የዚህ ሆቴል ቤት ሕንፃ 47 ፎቆች አሉት። ሆቴል ቤቱ ባንድ ጊዜ ሁለት ሺህ እንግዶችን የሚቀበሉ የመኝታ ክፍሎች አሉት። የምግብ ቤቱ ለፓርቲ ግብዣ ጊዜ 5.400 ሰዎች ይይዛል።

ሆቴል ቤቱ በ1959 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በወጣው መግለጫ በዚያ ዓመት በሆቴል ቤቱ ውስጥ ያለቁትን ምግብና መጠጦች ባጭሩ እንደሚከተለው ዘርዝሯል።

50.800 ኪሎ ወይም 50 ቶን ዶሮ 15.035 ጠርሙስ ሻምፓኝ 80.482 ጠርሙስ ውስኪ፤ ሶስት ሚሊዮን 500 ሺህ ስኒ ቡና መሸጡን አስታውቋል።

## የመጽሐፍት ሱቅ፤

በለንደን ከተማ ያለው የፎይሌ የመጻሕፍት መሸጫ ኩባንያ ሱቅ በዓለም ካሉት የመጻሕፍት መሸጫ ሱቆች ሁሉ ይበልጣል። በሱቁ አራት ሚሊዮን መጻሕፍት ይደረደራሉ። የመጻሕፍቱ መደርደሪያ ጠቅላላ ርዝመት ሠላሳ ማይል ነው። ወይም በሌላ አነጋገር የመጽሐፍ መደርደሪያዎቹ በቀጥታ ቢዘረጉ 30 ማይል ይረዝማሉ።

መጻሕፍት ቤቱ 600 ሠራተኞች አሉት፤ ባመት ዘጠኝ ሚሊዮን የመጻሕፍት መጠየቂያ ደብዳቤዎች ይደርሱበታል። ባመት የሚሸጠው የመጻሕፍት ብዛት አምስት ሚሊዮን ነው።

## የጫማ ሱቅ፤

በዓለም ትልቁ የጫማ ሱቅ በለንደን ከተማ በኦክስፎርድ ጎዳና ያለው ሊሌይ ኤንድ ስኪነር ሊሚትድ ነው። አምስት መቶ ሺህ ጥንድ ጫማዎች በሱቁ ውስጥ ይደረደራል። ለደንበኞች ጫማ አቅራቢ የሆኑ 250 ሠራተኞች አሉት። ባንድ ሳምንት ሠላሳ ሺህ ጫማ ገዢዎች ከሱቅ ይገባሉ።

## ጋራዥ

በዓለም ካሉት ጋራዦች (የመኪና መሥሪያ) ሁሉ ትልቁ በእንግሊዝ ሀገር በበርሚንግሃም ያለው የአውስቲን ሞተር ማደሻ ነው። 2.300 መኪናዎች የማቆሚያ ቦታ አለው። መኪናዎቹ የሚቆሙት ሁሉም ባንድነት በመሬት ተደርድረው ሳይሆን በዘጠኝ ፎቅ ላይ ተከፋፍለው ነው።

## አዳራሽ

በሮም ከተማ ያለው ኰሌሲዮም በትልቅነቱ ከሌሎች አዳራሾች ሁሉ ይበልጣል። ለሕዝብ የተከፈተው 1160 ዓመታት በፊት 80 ዓ.ም ነው። ይህ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች የሚታዩበት አዳራሽ ባንድ ጊዜ 385.000 ሰዎች ይይዛል።

ከዘመናውያን የጨዋታ ማያ አዳራሾች በትልቅነቱ የታወቀው በኒውጀርሲ ያለው አትላንቲክ የተባለው ነው። አትላንቲክ 41.000 ተመልካቾች ይይዛል።

## እስታዲዮም

በዓለም ካሉ እስታዲዮሞች ሁሉ ትልቁ በቼኰዝሎቫኪያ ዋና ከተማ በፕራግ ያለው ስትራሆቭ እስታዲዮም የተባለው ነው። የዚህ እስታዲዮም ሥራ የተጠናቀቀው በ1934 ዓ.ም ነው።

ይህ እስታዲዮም 240.000 ተመልካች ይይዛል። የመሐሉ ሜዳ ስፋት 40.600 ጅምናቲክ ሠራተኞች ባንድ ጊዜ ሊሠሩበት ይቻላሉ።

የእግር ኳስ መጫወቻ ከሆኑ እስታዲዮሞች ሁሉ ትልቁ በብራዚል ዋና ከተማ በሪዮደጀኔርዮ የሚገኘው ማራካና የተባለው የማዘጋጃ ቤቱ እስታዲዮም ነው። በዚህ እስታዲዮም 155.000 ሰዎች ተቀምጠው ጨዋታውን ለአምየት ሲችሉ ለ45.000 ሰዎች ድግሞ ቆሞ የማያ ቦታ አለው። በ1950 ዓ.ም ሐምሌ 1 ቀን የብራዚል ቡድንና የኡራጋይ ቡድን በዚህ እስታዲዮም ግጥሚያ ሲያደርጉ ጨዋታውን ለመመልከት የገባው ሰው 199.854 ነበር።

## ናይት ክለብ፤

ከናይት ክለቦች ሁሉቀደምትነት ያለው ወይም ከዛሬዎቹ ናይት ክለቦች ሁሉ አንጋፋው ለ ባል ዴ አንግሌ የተባለው ነው። ይህ ናይት ክለብ የሚገኘው በፈረንሣይ ዋና ከተማ በፓሪስ ነው። ክለቡ የተከፈተው ከዛሬ መቶ ሃያ ዓመት በፊት በ1843 ዓ.ም ነው።

በዓለም ካሉት ታላላቅ ናይት ክለቦች ሁሉ ብልጫ ያለው በኒዮርክ ከተማ የሚገኘው ኮንኮርድ የተባለው ነው። ይህ ናይት ክለብ ባንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ሰዎች ሊያስተናግድ ይችላል። በአሳላፊዎች ብዛት ደግሞ ትልቁ ናይት ክለብ በጃፓን ሀገር በኦሳካ ያለው ዘ ዩኒቨርስ የተባለው ነው። ዩኒቨርስ ባሉት 360 ጠረጴዛዎች አንድ ሺህ እንግዶችን ይቀበላል። ለነዚህ እንግዶች የተዘጋጁ አስተናባሪዎችና አሳላፊዎች አንድ ሺህ ናቸው።

በኩባ ዋና ከተማ በሐቫና ያለው ትሮፒካና የተባለው ናይት ክለብም በትልቅነቱ ዝነኛና የታወቀ ነው።

ሰዓት

በ725 ዓ.ም ኢ ሲንግ ፃን እና ሊንግ ቲንግ የተባሉ የቻይና ሰዎች ሰዓት ሠርተው እንደ ነበረ ይተረካል። በ1360 ዓ.ም ሔንሪ ደ ቬክ የተባለ ሰው የመጀመሪያውን ሰዓት ፈጠረ። ሰዓቱ 250 ኪሎ ይመዝን ነበር። የሰዓቱ መቁጠሪያም አንድ እጅ ብቻ ነበር። ከዚህም ሌላ ሰዓቱ ብዙውን ጊዜ በቀን ውስጥ ሁለትና ሦስት ሰዓት ያሳስት ነበር አሉ።

በ1581 ዓ.ም ጋሊልዮ ሌላ ፈጠረ። በ1629 ዓ.ም ክርስቲያን ሁጀንስ የተባለ ሰው የተሻለ ሥራ። የሱም ሰዓት ጊዜን በትክክል የሚቆጣጠር በመሆኑ

ተወደደ። ስለ ሰዓት አፈጣጠር ባጭሩ በዚሁ ቢበቃን ደህና ነው። አሁን ወደ አስደናቂዎቹ ሰዓቶች ሁኔታ እንመለስ።

በዓለም ካሉት ሰዓቶች ሁሉ ትልቁ በፈረንሣይ ሀገር ቢውቫይስ ካቴድራል ያለው ነው። የሰዓቱ ሥራ በ1865 ዓ.ም ተጀምሮ በ1868 ዓ.ም ተጠናቋል። ሰዓቱ 90.000 መሣሪያዎች አሉበት። ቁመቱ 40 ጫማዎች ወይም 26 ክንድ ነው። ስፋቱ ደግሞ 20 ጫማዎች ወይም 13 ክንድ ነው። የሰዓቱ ሆድ ማለት ጥልቀቱ ዘጠኝ ጫማ ወይም ስድስት ክንድ ነው።

በምክር ቤት (ፓርላማ) ላይ ከተደረጉ ሰዓቶች ሁሉ ትልቁ በኒውጀርሲ ከተማ ምክር ቤት ላይ ያለው ነው። ዙርያ ክቡ 50 ጫማ ወይም 32 ክንድ ነው። የደቂቃ ቆጣሪው እጅ 27 ጫማ ወይም 18 ክንድ ርዝመት አለው። ሰዓቱ ሥራውን የጀመረው በ1924 ዓ.ም ታኅሣሥ 1 ቀን በስድስት ሰዓት ላይ ነው።

ለእጅ ሰዓቶች ሁሉ ውዱ በስዊዘርላንድ የሚሠራው አውዳማርስ ነው። በ1411 ያሜሪካን ብር ወይም በ3527 የኢትዮጵያ ብር ከሃምሳ ሳንቲም ተሸጧል። ሰዓት ከብዙ ጥቃቅን ክፍሎች የሚሠራ ነው። ለምሳሌ ትንሿ የሴት የእጅ ሰዓት 125 የመሣሪያ ዓይነቶች አሉበት።

## <u>ፎቶ ግራፍ፤</u>

የመጀመሪያው ፎቶ ግራፍ የተነሳው በ1826 ዓ.ም ነው። ያነሳው ጀሴፍኒስፍሬ የተባለ የፈረንሣይ ሣይንቲስት ነው። ስለ ፎቶ ግራፍ ሥራ አፈጣጠር ብዙ ተደክሞበታል። ከስዊድኑ ሊቅ ከካርል ዊልያም ሺሌ ከ1777 ዓ.ም እጅምሮ ሲጠናና ሲሞከር የኖረ ነው።

ከዐየር ላይ ሆኖ የሚነሳው ፎቶ ግራፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳው በ1858 ዓ.ም ፌሊክስ በተባለ ሰው ነው። የተነሳውም ፎቶ ግራፍ ከፓሪስ ከተማ አንድ ክፍል ነው።

## መጠጥ፤

ቢራን መጥምቅ የጀመሩ የባቢሎን ሰዎች ናቸው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4000 ዓ.ም ወይም እከዛሬ 5.966 ዓመታት በፊት የባቢሎን ሰዎች አሥራ ስድስት ዓይነት ቢራ ይጠምቁ ነበር።

ወይን ጠጅ በእንዱስርቲ መልከ መሠራት ከጀመረ ጊዜው ቆይቷል። ወይን ጠጅን ለመጀመሪያ ጊዜ በእንዱስትሪ ለመሥራት ዘዴውን ያገኙት ባፓሌስታይን ውስጥ ኢልጂባ በተባለች መንደር የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ወይን ጠጅን በእንዱስርቲ መልከ መሥራት የጀመሩት ከዛሬ 2600 ዓመታት በፊት ነው።

አሁን ካሉት መጠጦች ሁሉ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣው የፈረንሣይ ወይን ጠጅ ነው። ቻቲላፊቴ ይሉታል። አንዱ ጠርሙስ 500 የፈረንሣይ ፍራንክ ይሸጣል። ፍራንኩ በኛ ብር ሲመነዘር 255 ብር ይሆናል።

## ጋዜጣ

የጋዜጣ ሥራ የተጀመረው ከአራት መቶ ዓመታት በፊት በ1566 ዓ.ም በጣሊያን ሀገር ነው። መጀመሪያ ጊዜ በብትን ወረቀት ላይ አንዳንድ ወሬዎች እየተጻፉ በመንገድ ላይ በመለጠፍ ሕዝብ እንዲያነባቸው ተደረጉ። እነዚህ ወሬዎች ለሕዝቡ ስለጣሙት በመንገድ ላይ ቆሞ በማንበብ ፋንታ ጋዜታ በተባለ ቤሳ እየገዙ ማንበብ ተጀመረ። በዚህ ሰበብ ስሙምም ጋዜታ ተባለ።

የወሬው መነበብ ተወዳጅ እየሆነ በመሔዱ በዕትመት ይደራጅ ጀመር። ጉዳዩም ወዲያው በኤሮፕ ታላላቅ ከተሞች ተዛምቶ ጋዜጦች በያገሩ ተቋቋሙ። በእንግሊዝ ሀገር የመጀመርያው ጋዜጣ በ1622 ዓ.ም ዊክሊ ኒውስ (ሳምንታዊ ዜና) በመባል መታተም ጀመረ።

## መጻሕፍት

የማተሚያ መሣሪያ ከተፈለሰፈበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዓለም የታተሙ መጻሕፍት አርእስት ብዛት 18 ሚሊዮን ነው። ይህ ቁጥር

የየመጽሐፉ ኮፒ ብዛት ሳይሆን አርእስታቸው ብቻ ነው። አንዱ መጽሐፍ ማለት አንድ አርእስት ያለው እስከ ሃያ ሚሊዮንም ሊታተም ይችላል።

መጻሕፍት መታተም ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ምን ያህል ኮፒዎች እንደታተሙ በእርግጥ አይታወቅም። ሊቃውንት በመሐከላቸው ግምት (አብሬጁ) እያንዳንዱ መጽሐፍ ሶስት ሺህ ኮፒዮች እንደታተመ አድርገው እያሰቡ የመጻሕፍቱን ብዛት 54 ቢሊዮን ያደርሱታል።

## ማኅበር

በዓለም ካሉ የግል ማኅበሮች ሁሉ የአሜሪካን የቀይ መስቀል ማኅበር በአባሎች ብዛት ተወዳዳሪ የለውም። ማኅበሩ የተቋቋመው በ1881 ዓ.ም ነው። 1962 ዓ.ም 44 ሚሊዮን 100 ሺህ አባሎች ነበሩት።

## የሠራተኞች ማኅበር

በዓለም ካሉ የሠራተኞች ማኅበሮች ሁሉ የምዕራብ ጀርመን የብረታ ብረት ፋብሪካ ሠራተኞች ማኅበር አንደኛ ነው። ማኅበሩ በ1961 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን 842.800 አባሎች ነበሩት።

እስከዛሬ በዓለም ከተደረጉት የሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ውስጥ በደንማርክ የኰፔንሐገን ከተማ ጠጉር ቆራጮች (አስተካካዮች) ያደረጉትን ሥራ ማቆም አድማ የሚወዳደር የለም። አድማው ሥራቸውን ባቆሙ በሰላሳ ሶስት ዓመት በ1961 ዓ.ም የካቲት 4 ቀን እንደ ገና ሥራቸውን ጀመሩ።

## ሕንፃ

በዓለም ካሉት ረጃጅም ሕንጻዎች ሁሉ የሚበልጠው በኒዮርክ ከተማ ያለው ኢምፓየር ስቴት ቢልዲንግ የተባለው ነው። ሕንፃው የተሠራው በሁለት ኤከርስ ቦታ ነው። ርዝመቱ 1472 ጫማዎች ወይም 980 ክንድ ነው። ይህ ርዝመት ጫፉ ላይ ካለው የቴሌቪዥን ጣቢያ ጭምር ነው።

ሕንፃው 102 ፎቆች አሉት። 6.500 የሆኑትን የሕንፃውን መስኮቶች ከሚወለውሉት ጋር በሕንፃው ውስጥ ሃያ ሽህ ሠራተኞች አሉ። በሕንፃው 36 የፎቅ መውጫ አሳንሰር ወይም ሊፍቶች አሉ። በእግር ለመውጣት ቢፈልግ 1860 ደረጃዎች አሉ። ይህ ሕንፃ የፈጀው ገንዘብ 42 ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ወይም 105 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው።

ሕንፃው ተሠርቶ ያለቀው ግንቦት 1 ቀን 1931 ዓ.ም ነው። በሕንፃው ጫፍ ላይ ሆኖ ሃምሳ ማይል ርቀት ድረስ ለማየት ይቻላል። ሐምሌ 28 ቀን 1945 ዓ.ም ቢ - 25 የተባለ ቦንብ ጣይ አኤሮፕላን ከሕንፃው ጋር ተጋጭቷል። በዚህ አደጋ 25 ሰዎች ሲቆስሉ 14 ሰዎች ሞተዋል።

ከዚህ ሕንፃ ቀጥሎ በርዝማኔ የሁለተኛነትን ደረጃ ይዘው በግሪንላንድ ያለው ነው። የግሪንላንዱን 1345 ጫማዎች ወይም 896 ክንድ ርዝማኔ ይረዝማል።

የሶስተኛነቱን ደረጃ የሚያዘው በጃፓን ዋና ከተማ በቶኪዮ ያለው የቴሌቪዥን ታወር ነው። ርዝመቱ 1089 ጫማዎች ወይም 726 ክንድ ነው። እስካሁን ስለ ረዥም ሕንፃዎች ተነጋገርን። አሁን ደግሞ በትልቅነት ማለት በግዙፍነት በዓለም የታወቁትን እንወቅ።

በቬርጂንያ አንድ ታላቅ ሕንፃ አለ። ሕንጽሳው የተሠራው ለመከላከያ ክፍል ቢኖርነት ነው። ሕንጽሳው ተሠርቶ ያለቀ በ1943 ዓ.ም ጥር 15 ቀን ነው። የፈጀውም ገንዘብ 83 ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ወይም 207 ሚሊዮን 500 የኢትዮጵያ ብር ነው። ይህ ሕንፃ በግዙፍነት በዓለም ተወዳዳሪ የለውም።

የሕንፃው ቁመት ረጅም አይደለም። 921 ጫማ ወይም 614 ክንድ ነው። አምስት ፎቆች አሉት፤ የወለሉ ጠቅላላ ስፋት ስድስት ሚሊዮን ተኩል እስኩየር ፊት ነው። በቀን 29 ሺህ ሰዎች ይወሉበታል። 44 ሺህ ቴሌፎኖች አሉበት። በቤቱ ውስጥ የተዘረጋው የቴሌፎኖቹ መስመር (ገመድ) 16000 ማይል ርዝመት አለው። በቀን 280.000 ጥሪ ወደ ሕንፃው ይደርሳል። ሁለት የምግብና 16 ቡና ቤቶች አሉት።

ከንግድ ሕንፃዎች ደግሞ በዓለም ታላቁ ሕንፃ ቺካጐ ውስጥ ያለው ዘ ሜርቸዲስ ማርት የተባለው ነው። ተሠርቶ ያለቀው በ1931 ዓ.ም ነው። የፈጀው ገንዘብ 32 ሚሊዮን ያሜሪካ ብር ወይም 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው።

የወለሉ ጠቅላላ ስፋት አራት ሚሊዮን 23.400 እስኩየር ፊት ነው። በቀን ሃያ ሺህ ሰዎች ይሠሩበታል። የሕንፃው ባለቤት ጆሴፍ ፒ ኬኔዲ ናቸው።

*********

# መገናኛ፤

## አኤሮፕላን

የመጀመሪያው አኤሮፕላን የበረረው በ1903 ዓ.ም ታህሣሥ 17 ቀን ነው። አኤሮፕላኖች ውቅያኖሶችን ማቋረጥ የቻሉት በ1919 ዓ.ም ከግንቦት 16 እስከ 27 ቀን ድረስ ነው።

የመጀመሪያው ጄት የበረረው ነሐሴ 27 ቀን 1939 ዓ.ም በጀርመን ሀገር ነው።

እስከ ዛሬ በዓለም ከተሠሩት አኤሮፕላኖች ሁሉ በግዙፍነት ተወዳዳሪ የሌለው ኸርክለስ የተባለው አኤሮፕላን ነው። የሠሩ አሜሪካኖች ናቸው። አኤሮፕላኑ የጀልባነትም ጠባይ ነበረው። ሞተሮቹ ስምንት ናቸው። ክብደቱ 213 ቶን ነው። አኤሮፕላኑ በኅዳር ወር 1974 ዓ.ም በሎስ አንጀሎስ ከተማ ለሙከራ በረራ ተነሣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ አረፈ። ያን ግዙፍነቱን ይዞ ዳግመኛ አልበረረም።

በአኤሮፕላን ታሪክ ውስጥ ሳያርፍ ረጅም ጉዞ ያደረገ ከአሜሪካ አየር ኃይል ውስጥ ቢ52 የተባለው አኤሮፕላን ነው። ጥር 16 ቀን 1957 ዓ.ም ከካሊፎርኒያ ተነስቶ ጥር 18 ቀን ተመለሰ። አኤሮፕላኑ የተመለሰው 24.325 ማይ ሳያርፍ ተጉዞ ነው። ይህን ርቀት የተጓዘው በ45 ሰዓት ከ19 ደቂቃ ነው።

ለአኤሮፕላኑ በዓየር ነዳጅ የሚሞሉለት ቢ ሲ 47 የተባሉ አኤሮፕላኖች ናቸው። አኤሮፕላኑ በበረራው ጊዜ ይጓዝበት የነበረው ፍጥነት መሐከለኛ ግምት (አቨሬጅ) በሰዓት 525 ማይል ነበር።

ወደ ላይ ከፍታ በመውጣት ከፍተኛነቱን ደረጃ የያዘው የመስኮቦች ዬ66 አ የተባለው አኤሮፕላን ነው። በ1961 ዓ.ም በሚያዝያ ወር ሌ/ኰሎኔል ጆርጊ ሞሰሎቭ እየነዳው 113.892 ጫማዎች ወይም 21 ማይል ከ57 ሜትር ከምድር ከፍ ብሎ ወጥቷል።

ከሔሊኮፕተሮች ዘር ትልቁ የሶቪየቶቹ ነው። የሶቪየቶቹ ወይም እንደ ሀገራችን አጠራር መስኮቦቹ ሚል ሚ6 የሚሉት ሔሊኮፕተር 42 ቶን ወይም 42672 ኪሎ ክብደት ተሸክሞ ይበራል። የሰባ አምስት ሰዎች መቀመጫ አለው።

በሔሊኮፕተሮች አመጣጠቅ በበላይነት የተመዘገበው 36.027 ጫማዎች ከፍታ ነው። ይህን የመምጠቅ ሬኮርድ የያዘው በ1958 ዓ.ም ሰኔ 13 ቀን የመጠቀው ጂቡሌት የተባለው ሰው ነው።

## ጉዞ

በአኤሮፕላን በመጓጓዝ አሜሪካኖችን የሚያህል የለም። በ1961 በአሜሪካ አገር የወጣው የአኤሮፕላን ጉዞ መግለጫ የአሜሪካ አኤሮፕላኖች ባንድ ዓመት 39 ሚሊያርድ 827 ሚሊዮን 300 ሺ የመንገደኞች ማይል መመላለሳቸውን ይናገራል። ይህን ጉዞ ለእያንዳንዱ የአሜሪካ ሕዝብ ብንደለድለው ላንድ ሰው 217 ማይል የአኤሮፕላን ጉዞ ይደርሰዋል። በዘመኑ የነበረ የአሜሪካ ሕዝብ ብዛት 183 ሚሊዮን 724 ሺህ ነበር።

## ጣቢያ

በዓለም ካሉ የአኤሮፕላን ጣቢያዎች ሁሉ ትልቁ በኒውዮርክ ከተማ ያለው ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ነው። ስፋቱ 4.900 ኤከርስ ወይም 122 ጋሻ ተኩል ነው።

ሥራ የሚበዛበት ጣቢያ የቺካጐው ነው። 1959 ዓ.ም 431.600 አኤሮፕላኖች አስተናግዷል። ከ49 ሰከንድ ውስጥ አንድ አኤሮፕላን ያርፋል ወይም ይነሳል ማለት ነው። ከዚያ የሚቀጥለው የሎስ አንጀለስ አኤሮፕላን ጣቢያ ነው። ባመት 324 ሺህ አኤሮፕላኖች ይስተናገዱበታል።

## ባቡር

በ1556 ዓ.ም በጀርመን ሀገር በማዕድኖች ቦታ የሚሠሩ በሐዲድ ላይ የሚሔዱ ካሚዮኖች ወይም ባቡር መሣይ ነገሮች ነበሩ። አንዳንድ ሊቃውንት የመጀመሪያዎቹ ባቡሮች እነዚያ ናቸው ይላሉ።

በ1771 ዓ.ም ተወልዶ በ1833 ዓ.ም የሞተው የደቡብ ዌልስ ተወላጅ የሆነው ሪቻርድ ትሬቪቲክ በጐታች (በፋልቱ) የሚሔደውን ባቡር ፈልስፎ በ1804 ዓ.ም ጥር 13 ቀን አስመርቋል።

የመጀመሪያው የሐዲድ መስመር ከእስቶክተን እስከ ዳርሊግተን ተዘርግቶ የመጀመሪያው ረጅም ተጓዥ ባቡር በመስከረም 27 ቀን 1825 ዓ.ም በሰዓት 15 ማይል እየሮጠ ተጉዟል፤ ይህ ባቡር በጆርጅ እስቴፈንስን ተሻሽሎ የተሠራ ነው።

የመጀመሪያው የመንገድኞች ማመላለሻ ባቡር ሥራ የጀመረው በዚያው በእንግሊዝ ሀገር ከማንቸስተር እስከ ሊቨር ፑል በተዘረጋው መስመር ላይ በመስከረም ወር 1830 ዓ.ም ነው።

የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ ባቡር ደግሞ ሥራውን የጀመረው በጀርመን ሀገር በበርሊን ከተማ 300 ያርድ ርዝመት ባለው ሐዲድ ላይ 1879 ዓ.ም ነው።

## ጣቢያ

በዓለም ካሉ ጣቢያዎች ሁሉ እጅግ በጣም ሥራ የሚበዛበት በእንግሊዝ ደቡባዊ ቀበሌ ያለው ክላፍም የተባለው ባቡር ጣቢያ ነው። በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ 2.500 ባቡሮች ያስተላልፋል።

በመንገድ ብዛት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው የባቡር ጣቢያ የቶኪዮ ከተማ ነው። በቀን አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ መንገደኞች ያስተናግዳል።

የሐዲድ መስመር

በባቡር ሐዲድ ርዝመት በኩል ብልጫ ያለው የአሜሪካ መንግሥት ነው። በአሜሪካ ሀገር ያለው የባቡር ሐዲድ ርዝመት 218.399 ማይል ነው።

# መኪና

## <u>አውቶሞቢል</u>

ፈጣን አውቶሞቢል ብሉበርድ የተባለው ነው። ብሉበርድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሠራ ሥራው አምስት ዓመት ፈጅትዋል። የመጀመሪያው ብሉበርድ አውቶሞቢል የአራት ሺህ አንድ መቶ ፈረስ ጉልበት ነበረው አሉ።

የመኪናው ክብደት 3.300 ኪሎ ነበር። ርዝማኔው ሰላሣ ጫማ ወይም ሃያ ክንድ ነበር። 1960 ዓ.ም መስከረም 16 ቀን ለሙከራ በሰዓት 576 ኪሎ ሜትር ሲበር ተገልብጦ ተሰባብረ። የተገለበጠው ሾፌሩ አወቶሞቢሉን መቆጣጠር ስላቃተው ነው። እንደ ገና ተሠርቶ በ1963 ዓ.ም በሰዓት 776 ኪሎ ሜትር ለመብረር ችሏል።

ከአውቶሞቢሎች ሁሉ ትልቅ ቀይም በአውቶሞቢል ታሪክ ውስጥ እስካሁን በትልቅነት የበላይነቱን (ሬኮርዱን) የያዘው ቡጋቲ ሮያሌ የተባለው ነው። የዚህ አውቶሞቢል ዘር የተሠራው ስድስት ብቻ ነው። የመጀመሪያው አውቶሞቢል የተሠራው በ1927 ዓ.ም ነበር። አውቶሞቢሉ ስምንት ስሌንደር ነበረው።

በጣም ውድ አውቶሞቢል ሮልስ ፎይስ ነው። ከሮልስሮይስ ሞዴሎች ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ቪ ሞዴል ነው። ሰባት ሰዎች ይይዛል። ዋጋው 27.600 ያሜሪካ ብር ወይም 69.000 የኢትዮጵያ ብር ነው።

በርከት ተደርጎ አልተሠራም እንጂ በአውቶሞቢል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ያወጥዋ ዴይተን የተባለው ነው፤ የ525 ፈረስ ጉልበት አለው፤ ጥይት አይበሳውም፤ በሾፌሩና በጌትዬው መሐል ያለው መስተዋት ከኋላ ጥይት ቢተኰስ ሾፌሩ አይሰማም። ሚስጢር እንዳይሰማ መስተዋቱ ይከላከላል ማለት ነው።

አውቶሞቢሉ ሁለት ራዲዮ፤ ቴሌቪዥን፤ የምግብና መጠጥ ማቀዝቀዣ (ፍሬዢደር) የብዙ ዓይነት መጠጦች ማስቀመጫ ጓዳና ሌላም ብዙ ጠቃሚ ነገሮች አሉበት። ዋጋው 75 ሺህ ያሜሪካ ብር ወይም 187.500 የኢትዮጵያ ብር ነው።

## አውቶብስ

በ1959 ዓ.ም በግንቦት ወር ሞስኰቦች ያወጡት 38 ክንድ ርዝማኔ አለው። ባንድ ጊዜ ሁለት መቶ ሰዎች ይይዛል።

## ካሚዮን

ፈረንሣዮች ለሰሀራ በረሀ ማልሚያ የሚሠሩት ካሚዮን በዓለም ካሉት ካሚዮኖች ሁሉ በግዙፍነት ይበልጣል። ካሚዮን ሞዴል ቲ 100 ነው። 12 ሲሊንደር አለ። 89 ቶን ወይም 90.424 ኪሎ ይጭናል። ይህን ክብደት በሚጭንበት ጊዜ የመኪናው ጠቅላላ ክብደት 187 ቶን ወይም 189.992 ኪሎ ይሆናል።

በዓለም ካሉ ረጃጅም ካሚዮኖች ሁሉ ብልጫ ያለው ደግሞ ያሜሪካን ጦር ሠራዊት ያሠራው ሎንግቪው የተባለው ነው። 54 እግሮች አሉት። የመኪናው ርዝመት 572 ጫማዎች ወይም 380 ክንድ ነው። የመኪናው ነጠላ ክብደት 450 ቶን ወይም 457.200 ኪሎ ነው።

እዚህ ላይ አንድ ልናውቀው የሚገባ ነገር አለ። በግዙፍነቱ በዓለም አንደኛ ነው ካልነው ካሚዮን ክብደት የዚህኛው ይበልጣል። ያኛው በግዙፍነቱ ከካሚዮኖች ሁሉ አንደኛ የሆነው ቁመቱ እንደ ሌሎቹ ካሚዮኖች ሁሉ አጭር ሆኖ ባለው ክብደት መሠረት ነው። ይሄኛው ግን እርዝማኔው ከሌሎቹ

ዝርያዎቹ ጋር ስለማይመጣጠን በእርዝማኔ እንጂ በግዙፍነት ከሌሎቹ ካሚዮኖች የበላይ ሊሆን አይችልም። ከተግባባን ወደዚሁ ወደ ረጅሙ ካሚዮን ታሪክ እንመለስ።

የካሚዮኑ የመጨረሻ ፍጥነት በሰዓት ሃያ ማይል ወይም 32 ኪሎ ሜትር ነው። ካሚዮኑ የሚነዳው በስድስት ሰዎች ነው። አንድ የሚሞላው ቤንዚን 7828 ጋሎን ወይም 46.968 ሊትር ነው።

## መንገድ

ከመንግሥታት ሁሉ የአሜሪካ መንግሥት በሀገሩ ውስጥ ያሠራው የመኪና መንገድ ብልጫ አለው። በአሜሪካ ሀገር ሶስት ሚሊዮን 545 ሺህ 693 ማይል ርዝመት ያላቸው መንገዶች አሉ።

## የመኪና ብዛት፤

በ1962 ዓ.ም በመላው ዓለም 132 ሚሊዮን መኪናዎች ነበሩ። ከአገሮች ሁሉ በመኪና ብልጫ ያለው ያሜሪካ መንግሥት በዚያ ዘመን 78 ሚሊዮን 631 ሺህ መኪናዎች ነበሩት፤ በአሜሪካ ሀገር እንደ መኪናው መብዛት የመኪናም ሌባ ሞልቷል። በዚያው ዓመት ማለት 1962 ዓ.ም በአሜሪካ አገር በመኪና ሌብነት ብቻ የታሠሩ ሰዎች 463 ሺህ ናቸው።

በ1964 ዓ.ም ደግሞ በአሜሪካ ሀገር መኪና ሠርቀው ከታሠሩት ሰዎች መሐል 4.115 ሴች በመኪና ሌብነት ተይዘው ታስረዋል።

## ብስክሌት

ብስክሌት የተፈለሰፈው በ1818 ዓ.ም ነው። ብስክሌትን የፈለሰፈው ቢሮን ካርክ የተባለ ጀርመናዊ ነው። ከባሮን ካርክ ቀጥሎ ኪርክፖትሪክ ማክሚላን የተባለ ሰው በ1839 ዓ.ም አሻሻለው። ፈረንሳዊ ኧርንስት ፒር በ1861 ዓ.ም ያሁኖቹን ዓይነቶቹን ብስክሌቶች አሻሽሎ ሠራ።

በብስክሌቶች ታሪክ ውስጥ እስከዛሬ በዓለም ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ረጅም ብስክሌት በ1898 ዓ.ም በማሳቹሴ ስ ከተማ የዋልታም ኩባንያ የሠራው ኦሪተን የተባለው ብስክሌት ነው።

ብስክሌቱ 23 ጫማዎች ከዘጠኝ ኢንች ወይም 16 ክንድ ርዝማኔ አለው። አሥር ኮርቻዎች ስላሉት ባንድ ጊዜ አሥር ሰዎች ያስቀምጣል። ለአሥሩም ሰዎች አሥር ፔዳሎችና አሥር የጅ መጨበጫ (መሪ) አለው። እግሮቹ ግን ሁለት ብቻ ናቸው።

አንድ ቶን ወይም አንድ ሺህ 16 ኪሎ ለመሸከም ይችላል። የብስክሌቱ ነጠላ ክብደት 152 ኪሎ ነው።

ዛሬ በዓለም ላይ ካሉት የብስክሌት ፋብሪካዎች ሁሉ ብልጫ ያለው በእንግሊዝ ሀገር በኖትንግሃም ያለው የብስክሌት ፋብሪካ ባመት ሁለት ሚሊዮን ብስክሌቶች ሠርቶ ያወጣል። ይህ የብስክሌት ፋብሪካ 9.005 ሠራተኞች አሉት።

# ስልክ

ስልክን የፈጠረ አሌክሳንደር ግርሃም ቢል ነው። አሌክሳንደር ግርሃም ቢል ስልክን ፈጥሮ በፈጣሪነት የምስክር ወረቀቱን (ፓቴንት) የተቀበለው መጋቢት 7 ቀን 1876 ዓ.ም ነው።

ከአሌክሳንድር በፊት አሥር ሰዎች ስልክን ለመፍጠር ሞክረው ነበር። ከነዚህም አንዱ ጀርመናዊው ፊሊፕ ሬይስ ነው። ከአሌክሳንደር ፈጠራ 13 ዓመታታ በፊት ፊሊፕ በ1863 ዓ.ም የስልክን ዘዴ ፈጥሮ የፈጣሪነት ወረ (ፓቴንት) ተቀብሎ ነበር። ፍሊፕ የሠራው ልክ እንደአሌክሳንደር ዓየንት እንደ ነበር ይተረካል። የፍሊፕ ሞዴል ዛሬ በደለን ከተማ በሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ለሕዝብ ይታያል። ስለ ስልክ አፈጣጠር ባጭሩ በዚሁ ይበቃል።

# ብዛት

በዛሬው ዓለም በስልክ ብዛት አሜሪካ አንደኛነቱን ደረጃ ይይዛል። በ1966 ዓ.ም የወጣው መግለጫ እንደሚያስረዳው በአሜሪካ 96 ሚሊዮን 193.200 ስልኮች አሉት።

በኤሮፓ 53 ሚሊዮን 377.600 በእስያ 15 ሚሊዮን 475.400 በአፍሪካ ሁለት ሚሊዮን 241.500 ሥልኮች አሉ ፡

በስልክ በመጠቀም የዓለምን የበላይነት ደረጃ የያዙት ካናዳውያን ናቸው። በካናዳ በዓመት የሚደረገው የቴሌፎን ግልጋሎት ለሕዝቡ ሲከፈል ለያንዳንዱ ካናዳዊ በነፍስ ወከፍ 551 የስልክ ግልጋሎት ይደርሰዋል። የአሜሪካ የስልክ ግልጋሎት ለሕዝቡ ሲከፈል በነፍስ ወከፍ 259 ጥሪ ይደርሳል።

# ፖስታ

የመጀመሪያው የፖስታ ቴምብር የወጣው በ1840 ዓ.ም ግንቦት አንድ ቀን በእንግሊዝ ሀገር ነው። በቴምብሩ ላይ ያለው ስዕል የንግሥት ቪክቶሪያ ነበር።

በዓለም ካሉት የፖስታ ቴምብሮች ሁሉ 1913 ዓ.ም በቻይና ሀገር የወጣውን ቴምብር በትልቅነት የሚወዳደረው እስካሁን አልታተመም። የቴምብሩ ትልቅነት ዘጠኝ ኢንች በሁለት ኢንች ነበር።

ትንሺቱ የፖስታ ቴምብር በ1863 ዓ.ም በኰሎምቢያ ቦሊቫር የታተመችው ናት። ዋጋዋ አሥር ሳንቲም ነው። ወርድና ቁመትዋ ግን 5/16በ3/8 ኢንች ነበር።

********

## ግብርና።

ብዙዎች የግብርና ተግባር መቼ እንደ ተጀመረ አያውቁም። ሊቃውንት ግን የብርና ተግባር የተጀመረበት ጊዜ አውቀው አውጀዋል። ሊቃውንቶቹ እንደሚሉት የግብርና ሥራ የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት 6750 ዓመተ ዓለም ላይ ነው።

እርሻን በመጀመሪያ የጀመሩት የኢራክ ሰዎች ናቸው ይባላል። መሬትን ቆፍሮ እህል መዝራት የተጀመረው ጃርም በተባለ ሀገር ነው። ጃርም በኢራክ ውስጥ የሚገኝ ነው።

የቤት እንስሳትም ቢሆኑ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምረው ከሰው ጋር ተላምደው አልኖሩትም። ቀስ በቀስ ከሰው ጋር መላመዳቸውን የተመራማሪዎች ሊቃውንት ጽሑፍ ይገልጻል እነዚህም እንስሳት ከሰው ጋር መኖር የጀመሩት መቼ እንደ ሆነ «እንስሳትና አራዊት» በሚለው ምዕራፍ አወራዋለሁ።

## እርሻ

በዛሬው ዕለት በዓለም ካሉት እርሻዎች ሁሉ ብልጫ ያለው በሶቪየት ኅብረት ውስጥ ያለ የማኅበር እርሻ ነው። የእርሻው ስፋት 60 ሺህ ኤክር ወይም አንድ ሺህ አምስት መቶ ኩታ ገጠም ጋሻ ነው።

ከግል እርሻዎች በካናዳ ውስጥ ሌት ብሪጅ ያለው የግል ስንዴ እርሻ በስፋቱ በዓለም ካሉ የግል እርሻዎች ሁሉ የበለጠ ነው። የእርሻው ስፋት 35 ኤክር ወይም 875 ጋሻ ነው።

## ከብት

እስከ ዛሬ በዓለም ከተገኙት ኮርማዎች ሁሉ ማክ የተባለውን ኮርማ የሚወዳደር አልተገኘም። በማሳቹሴትስ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኦቬሪይ ኮርማ ነው። ኮርማው ከእበት መጣያው እስከ አፍንጫው አሥራ አንድ ክንድ ይረዝማል። ክብደቱ ደግሞ 2314 ኪሎ ነበር።

# እንስሳትና አራዊት

እንስሳት ለማዳ መሆን የጀመሩት ከክርስቶስ በፊት በአምስት ሺህ ዓመተ ዓለም ላይ ነው። ከዛሬ 6.900 ዓመታት በፊት ማለት ነው። እንስሳት ለመጀመሪያ ጊዜ ለማዳነት የጀመሩት በሰሜናዊ ኢራክ ውስጥ ባናሒልክ በተባለ ቦታ መሆኑን ሊቃውንት ይናገራል።

እንስሳት በሙሉ በአንድ ጊዜ ከሰው ጋር ተላምደው መኖር አልጀመሩም። ቀስ በቀስ እየቆዩ ነው። ለምሳሌ ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን በፊትና በኋላም መልመድ የጀመሩ አሉ። ሊቃውንት ግን መሐከለኛ ብለው ያወጡት የዘመን ግምት የላኛው ነው።

## በግ

በግ ከሰው ጋር መኖርን የጀመረው በ8800 ዓመተ ዓለም ላይ ነው። ከዛሬ 10.760 ዓመታት በፊት ማለት ነው።

በግን ለማዳ ያደረጉት የግብርና ሥራ የጀመሩት ኢራኮች ናቸው ይባላል። ይባላሉን ካረዘምነው በግ ለማዳነቱን የጀመረው ዛዊ ቸሚ ሻኒዳር በተባለ አውራጃ ነው። ከቤት እንስሳት ሁሉ የመጀመሪያው ለማጅ በግ መሆኑ ይነገራል።

በበግ ታሪክ ውጽጥ በዋጋ ብልጫ የበላይነቱን የያዘው በ1962 ዓ.ም በደቡብ አውስትራሊያ ተራራ ላይ የጆን ክሊንስ ኩባንያ አርብቶ የሸጠው አንድ በግ ነው።

ጢማሙ ጠጉራም በግ የተሸጠው በ10.500 ፓውንድ ወይንም 73.500 የኢትዮጵያ ብር ነው። የበግ ዕድሜ እስከ 12 ዓመት ድረስ እንው።

## ፍየል

ፍየል ከሰው ጋር ተላምዶ መኖር የጀመረው ከዛሬ 8.460 ዓመታት በፊት በ6.500 ዓ.ም ላይ ነው። ፍየል ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰው ጋር ለመኖር

መልመድን የጀመረው በኢራክ ውስጥ ጃርሞ እና ጄሪኮ በተባሉ አምባዎች ነው። የፍልየል ዕድሜ 15 ዓመት ነው።

## አሳማ

አሳማ ከሰው ጋር ተላምዶ መኖር የጀመረው በጃርሞ መንደር ከክርስቶ በፊት 6.500 ዓ.ዓ ላይ ነው። ከዛሬ 8.460 ዓመታት በፊት ማለት ነው።

የአሳማ ዕድመኢ 25 ዓመት ነው።

## ውሻ

ውሻ በ8000 ዓ.ዓ ገደማ በሜሶፔታሚያ ሰለቆ መታየት ጀመረ። ከዚያን ዘመን ጀምሮም ከሰው ጋር ተላምዶ መኖርን ጀመረ።

የውሻ ዕሜ 15 ዓመት ነው። ሃያ ዓመት ዕድሜ የሚያገኙ ውሾች ይደነእቃሉ። በውሻ ታሪክ ውስጥ በዕድሜ ትልቅነቱ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም የሚባለው አገዙታን የተባለ ውሻ ነው።

አገዙታን በአሜሪካ የቦስተን ነዋሪ የሆኑት የአቶ ጀምስ ውሻ ነው። አገዙታን ነሐሴ 14 ቀን 1936 ዓ.ም ተወለደ። በተወለደ 27 ዓመቱ በ1963 ዓ.ም ጥቅምት 20 ቀን ሞተ።

በክብደት የውሾችን የበላይነት የያዘ በአሜሪካ የካሊፎርኒያው ነዋሪ የአቶ ጃክ ቡዚባክ ውሻ ነው። ውሻው 123 ኪሎ ይመዝን ነበር።

በውሾች ሩጫ የውሾች ሁሉ ቀዳሚ የሆነው ሳሉክ የተባለ ውሻ ነው። ሳሉክ በሰዓት 68 ኪሎ ሜትር ከ800 ሜትር ሮጥዋል።

በዝላይ ደግሞ የውሾች ሁሉ የበላይ ሚኬሻ ነው። የእንግሊዝ ፖሊሶች ውሻ ነበር። በ1934 ዓ.ም በለንደን ከተማ በተደረገው የውሾች የዝላይ ውድድር ስድስት ክንድ ርዝመት ያለውን ግንብ ዘሏል።

## ላም

ላም ከሰው ጋር ተላምዳ መኖር ከጀመረች 6.900 ዓመታት አልፈዋል። ላም ከሰው ጋር ተላምዳ እምኖር የጀመረችው ከክርስቶስ በፊት በ5000 ዓ.ዓ ላይ ነው።

የላም ዕድሜ 25 ዓመት ነው። በላሞች ታሪክ ውስጥ በሽያጭ ዋጋ ከፍተኛነት የበላይነቱን የያዘችው ሾርዘን የተባለች ላም ነች። እንግሊዛዊው ወተት እንጋዴ አቶ ፓቪን ዳቪስ 1873 ዓ.ም በአርባ ሺሕ ስድስት መቶ ዶላር ወይም 1011500 የኢትዮጵያ ብር ሒሳብ ሾርዘን የተባለችውንላም ገዝቷል።

## ዶሮ

የዶሮ ዕድሜ 14 ዓመት ነው። በዶሮ ታሪክ ውስጥ ደግሞ በዕንቁላል አጣጣል የበላይነቱን ይዛ ትኖር የነበረች በደቡብ አፍሪካ ግሊን በሚባል የእርሻ ኰሌጅ ከነበሩት ዶሮዎች አንዷ ነበረች። ከ1944 ዓ.ም እስከ 1945 ዓ.ም ድረስ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማለት በ365 ቀናት 355 እንቁላሎች ጥላለች።

በኋላ በ1948 ዓ.ም «የሁሳርስ ሙሽራ» የተባለች አንዷት ዶሮ ባመት ማለት በ365 ቀናት 360 እንቁላሎች በመጣልዋ በእንቁላል አጣጣል የዓለም ዶሮዎች የበላይ ሆናለች።

ከእሷ በኋላ ደግሞ በ1957 ዓ.ም በጥር ወር በእንግሊዝ ሀገር የአቶ ቶማስ ዶሮ በስድስት ቀን 16 ዕንቁላል በመጣልዋ የዓለም ዶሮዎች የበላይ እንቁላል ጣይ ሆነች።

## ፈረስ

የፈረስ ዕድሜ በመሐከለኛ ግምት (አቬሬጅ) ሠላሳ ዓመት ነው። ከፈረስ ሁሉ ትልቅ ዕድሜ ያገኘው ቢሊ የተባለ ነው። ቢሊ ያንድ እንግሊዛዊ ፈረስ ነበር። 61 ዓመታት በሕይወት ቆይትዋል። ከቢሊ በፊት ያንድ ኢጣሊያዊ ፈረስ በዕድሜ ብዛት ይደነቅ ነበር። ጣሊያኑ ፈረሱን ቶፖሊኖ ይለው ነበር።

ቶፖሊኖ በ1909 ዓ.ም የካቲት 24 ቀን ሊብያ ውስጥ ተወልዶ በ53 ዓእምቱ በ1962 ዓ.ም በየካቲት ወር ብሬሺያ ውስጥ ሞተ።

ዶክተር ለ ጊር የተባለ ፈረስ ደግሞ ግዙፍ ነበር። በግዙፍነት ከፈረሶች ሁሉ የበላይ ነው የሚባለው ለ ጊር ነው። 1480 ኪሊ ይከብድ ነበር። ከአፍንጫው እስከ ፋንድያ መጣያው ያለው ርዝመት አሥራ አንድ ክንድ ሲሆን ቁመቱ ደግሞ አምስት ክንድ ነበር። ለ ጊር 1919 ዓ.ም በሳንት ሊውስ ሞተ።

በፈረስ ገበያ ደግሞ የእስኰትላንዱ ሰው አቶ አይር በ1911 ዓ.ም በታህሣሥ ወር የገዛው ፈረስ በዋጋ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም። ፈረሱ የተሸጠው በ26.390 ያሜሪካ ብር ወይም 67325 የኢትዮጵያ ብር ሒሳብ ነው።

## ድመት

ሊቃውንቶች የድመቶች ዕድሜ ከ21 ዓመት እስከ 30 ዓመት ይደርሳል ይላሉ። ድመቶች በስተርጅናቸውም ቢሆን ሊወልዱ ይችላሉ። ሴት ድመት በ26 ዓመት ዕድሜዋ ልትወልድ ትችላለች።

ሊቃውንት የድመትን ከፍተኛ ዕድሜ በሠላሳ ዓመታት ላይ ቢያቆሙትም የእንግሊዛዊትዋ አሊስ ሙር ድመት በ1957 ዓ.ም ኅዳር 5 ስትሞት ዕድሜ 35 ዓመት ነበር። እስከ ዛሬ ያለው የድመቶች ዕድሜ ሪኮርድ ወይም የበላይነት የወይዘሮ ሙር ድመት አንት።

## ዝሆን

ጨዋ አራዊት ነው። ከአራዊት ሁሉ ትልቅ አንጐል ያለውም እሱ ነው። የዝሆን አንጐል ሰባት ኪሎ ያህል ይመዝናል። ዝሆን ካስለመዱት ትእዛዝ ተቀባይና ሰሚ ነው። ሒድ፤ ቁም፤ ተነስ፤ ተኛ፤ ማለትን ብቻ ሳይሆን እግርህን አንሳ፤ በጐንህ ተኛ ጀርባህ ላይ ውሃ እርጭ ውሀ ውስጥ ግባ፤ በራስህ ያንን ነገር ግፋው ይህን የመሳሰሉትን ትእዛዞች ሁሉ ሊቀበል የሚችል አራዊት ነው። ዝሆን ለማደግ ብዙ ጊዜ ይወስድበታል። የዝሆን ዕድሜ 200 ዓመት ነው

የሚሉ አሉ። ብዙዎቹ ሊቃውንት ግን የተስማሙት የዝሆን ዕድሜ አንድ መቶ ዓመት ነው ብለው ነው።

ከዝሆኖች ሁሉ ትልቁ የአፍሪካ ዝሆን ነው። ፈረንጆች ሉክሶዳንታ አፍሪካና የሚሉት ዝሆን በቁመትና በክብደት ጓደኛም አላገኘ። የሽቅበት ርዝመቱ ስምንት ክድን ከስንዝር ነው። ክብደቱ ድግሞ 12 ቶን ወይም 12.192 ኪሎ ነበር። ይህም ዝሆን የተለካውና የተመዘነው በ1955 ዓ.ም አንጐላ ላይ ተገድሎ ዋሽንግተን ከተወሰደ በኋላ ነው።

## ቀጭኔ

የቀጭኔ ልብ ከማንኛውም አራዊት የሚበልጥ ትልቅና ደምን በኃይል የሚረጭ ነው። የቀጭኔ ልብ አመታት አንገትዋ ድረስ ያለውን እይዳገት ርቀት ደምን ለማስተላለፍ የሚችል ኃይለኛ ነው። የቀጭኔ አንገት ስምንት ክንድ 13 ጫማ ይረዝማል።

ከቀጭኔዎች ሁሉ በደቡብ ሰሃራ የሚገኙ ቀጭኔዎች ከሌሎቹ ቀጭኔዎች ይበልጣሉ። በደቡብ ሰሃራ የሚገኙ ቀጭኔዎች አሥራ ሶስት ክንድ ርዝማኔ አላቸው።

## ነብር

በአጭር ሩቻ ቺታህ የሚባለውን የነብር ዘር የሚወዳደር የለም። በሰዓት 114 ኪሎ ሜትር ይሮጣል። የነዚህ ቺታህ የተባሉ ዘሮች የአሯሯጣቸው መሐከለኛ ግምት በሰዓት 71 ኪሎ ሜትር ነው። በችታህና በፈረስ መሐል ላለው የሩጫ ልዩነት የፈረስ እሩጫ መሐከለኛ ግምት (አብሬጁ) በሰዓት 68 ኪሎ ሜትር የችታህ ግን 71 ኪሎ ሜትር ነው።

ቺታህ በብዛት የሚገኘው በመሐከለኛው ሕንድ ግዛት ነው።

# አዞ

አንድ ጊዜ በደቡብ ምሥራቅ እስያ አንድ አዞ ተይዞ ነበር። የአዞው ርዝመት 33 ጫማ ወይም 22 ክንድ ሆንዋል። የዚህ አዞ ጭራ 13 ጫማ ከስምንት ኢንች ወይም ዘጠኝ ክድን ያህል ሆንዋል።

አንድ ጊዜ ደግሞ በ1840 ዓ.ም አንድ አዳኝ ሰው አንድ አዞ ገድሎ ነበር። የተገደለው አዞ ቢመዘን ክብደቱ 3000 ኪሎ ሆንዋል። በአዞ ታሪክ ውስጥ ረጅምና ግዙፍ የሚባሉ እነዚህ ሁለቱ ናቸው።

ከአዞ ዘር ሁሉ ትንሽቱ የምትገኘው በማዳጋስካር ነው። የዚች ትንሽ አዞ ርዝመት አንድ ኢንች ተኩል ነው።

በጆርጂያ ከተማ የአዞች የሩጫ ውድድር ተደርጐ በተገኘው ውጤት ቀዳሚው አዞ በሰዓት 18 ማይል ወይም 28 ኪሎ ሜትር ከ800 ሜትር ሮጥዋል። የሩጫው ውድድር በውሀ ውስጥ ሳይሆን በመሬት ላይ ነበር። እስካሁን በአዞዎች የሩጫ ታሪክ ውስጥ ያን ሬኮርድ የሰበረ የለም። የአዞዎች ዕድሜ መሐከለኛ ግምት 300 ዓመት ነው።

# ኤሊ

አንድ ጊዜ በውቅያኖስ አካባቢ የተገኘው ኤሊ 954 ኪሎ መዝኗል። የዚህ ኤሊ ርዝመት ስድስት ክንድ ነበር። ኤሊው ሲጓዝ እንደዝርያዎቹ የሚቀረፈፍ አልነበረም። በሰዓት 22 ማይል መሮጥ ይችል ነበር።

በ1773 ዓ.ም ካፒቴን ኩክ ለንግሥት ሳሎቴ የሰጣቸው ኤሊ የሞተው በ1958 ዓ.ም ነው። ኤሊው 185 ዓመት ዕድሜ አግኝቷል ማለት ነው። ሊቃውንቶች እንደሚሉት የኤሊ ዕድሜ 350 ዓመታት ይደርሳል።

ማንም እንደሚያውቀው ኤሊ ቀረፈፍ እንጂ ፈጣን አውሬ አይደለም። በሰዓት 22 ማይል ተጉዟል ያለንው ኤሊ በኤሊዎች ታሪክ ውስጥ በሩጫ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ነው። የኤሊ የመጨረሻ አነስተኛ ሩጫ በደቂቃ አምስት ያርድ ነው።

# እባብ

እባብ ብዙ ዝርያ አለው። የእባብ ዝርያዎች 2400 ዓይነቶች ናቸው። ከነዚሁ ውስጥ ከፉዎቹ መርዘኞች ሁለት መቶዎቹ ናቸው። በእባብ መርዝ በያመቱ ብዙ ሰዎች ያልቃሉ። የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት እንደገለጸው በዓለም ባመት አርባ ሺህ ሰዎች በእባብ ንክሻ ይሞታሉ። እባቦች ብዙ ሰው የሚፈጅት በተለይ በሕንድ አገር ነው። አንድ ጊዜ ባንድ ዓመት ውስጥ ሃያ ሺህ ሰዎች በእባብ ተነድፈዋል።

ከእባብ ዘር ሁሉ በመርዘኛነታቸው የታወቁት ኮብራ ከተባለው የእባብ ዝርያ ውስጥ ሓማድርያድ የተባለው ነው። ይህ እባብ እንደ ኮብራ አጭር አይደለም። አንድ ጊዜ ሲያም በተባለ ሀገር ተገድሎ ቢለካ ርዝማኔው አሥራ ሁለት ክንድ ሆንዋል።

ከእባብ ዘር ሁሉ በበርማ ግዛት በማላይና በኢንዶ ቻይና የሚገኙት እባቦች በእርዝማኔያቸው የታወቁ ናቸው። አሥራ ስምንት ክንድ ያህል ይረዝማሉ። አጫጭር እባቦች የሚገኙት በደቡባዊ ምዕራብ አሜሪካ ነው። ከዚያ የሚገኙት እባቦች እርዝመት አራት ኢንች ነው።

እስከ ዛሬ ከእባብ ዘር ውስጥ በክብደት ተወዳዳሪ ያልተገኘለት በደቡብ አሜሪካ ውስጥ አንድ ጊዜ የተገኘው እባብ ነው። ይህ እባብ አሥራ ሶስት ክንድ ሲረዝም ክብደኡት 180 ኪሎ ነበር።

በእባብ ታሪክ ውስጥ ብዙ ዕድሜ ያለው ባለ ጥቁሩ ቅርፊት ኮብራ እባብ ነው። ይህ እባብ የሚገኘው በአፍሪካ ውስጥ ነው። በሳንዲያጐ የአራዊት ማኖሪያ (ዙ) ውስጥ ይሔው እባብ ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ተፈልፍሎ ኅዳር 12 ቀን 1957 ዓ.ም በተፈለፈለ 29 ዓመት ከአርባ ሁለት ቀናት ሞተ።

ማምባ የሚባለው እባብ ፈጣን ተወርዋሪ ነው። በሰአት ሰባት ማይል ወይም 11 ኪሎ ሜትር ከሁለት መቶ ሜትር ይወረወራል። እባቡ አደጋ ለመጣል ወይም ለመብረር በፈለገ ጊዜ በሰዓት 15 ማይል ወይም 24 ኪሎ ሜትር ለመፈናጠር ይችላል።

# እንቁራሪት

በጃፓን ሀገር አንድ ጊዜ አንድ እንቁራሪት ተገኝትዋል። እንቁራሪቱ አራት ክንድ ቁመትና 45 ኪሎ ክብደት ነበረ። በ1906 ዓ.ም በምዕራብ አፍሪካ የተገኘው አንቁራሪት ከጭራው እስከ ጭንቅላቱ 12 ኢንች እርዝማኔ ሲኖረው የወደላይ ርዝማኔው ቁምቱ ደግሞ ሁለት ጫማ (ፊት) ነበር።

ከቅንቁራሪቶች ዕድሜ ትልቁን የያዘው በኰፔንሀገን ዙ ውስጥ በ60 ዓመቱ የሞተው እንቁራሪት ነው።

በ1954 ዓ.ም ግንቦት 24 ቀን በካሊፎርኒያ የእንቁራሪቶች የዝላይ ውድድር ተደርጐ ነበር። በውድድሩ የአቶሮይ ዌይመር እንቁራሪት «ለኪ» ወይም በአማርኛ ዕድለኛ የተባለው እንቁራሪት አሥራ አንድ ክንድ ዘሎ አንደኛ ሆንዋል።

ከአንድ ዓመት በኋላ በ1955 ዓ.ም በግንቦት ወር በዚያው ቦታ በተደረገው የዕንቁራሪቶች የዝላይ ውድድር አንድ ከአፍሪካ የተላከ እንቁራሪት አሥር ክንድ ርዝመት ዘሏል።

# አሣ

ከአሣ ዘር አሣ ነባሪ ትልቅ መሆኑን እናውቃለን። ግን ትልቅነቱ እንዴት እንደ ሆነ ብዙዎች አናውቅም። በ1828 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ላይ ተይዞ የተላከው አሣ ነባሪ ርዝመቱ 30 ክንድ ነበር። ከዚህም የበላለጡ አሉ።

ከአሣ ነባሪ ታሪክ ውስጥ ትልቁ አርባ ክንድ ርዝማኔና 67 ቶን 68.072 ኪሎ ክብደት ያለው ነው። ይህን ያህል ክብደት ያለው አሣ ነባሪ የሚገኘው በአትላንቲክ በፓሲፊክና በሕንድ ውቅያኖሶች ውስጥ በሞቃቱ ክፍል ነው። ከቮልጋ ወንዝ ውስጥ ሞስኮቦች የያዙት አሣ ነባሪ 18 ክንድ ርዝማኔ ያለውና 16 ቶን ክብደት የነበረው ነበር። ከአሣ ዘር ውስት ትንሾቹ የሚገኙት በፊሊፒን ነው። ከእነኛ አሣዎች ትልቁ 11 ሚሊ ሜትር ርዝማኔ አለው። ክብደቱ ደግሞ ስድስት ሚሊ ግራም ነው።

በፍሎሪዳ በሰዓት 68 ማይል የሚሮጡ አሣዎች ተገኝተዋል። በካናዳ ውድ በተባለው ሐይቅ ውስጥ ሐምሌ 15 ቀን 1953 ዓ.ም አንድ አሣ ተያዘ። አሣው 107 ኪሎ ይመዝን ነበር። የአሣ ዕድሜ አጥኚ ጓድ የሆኑ ሊቃውንት የዚያ አሣ ዕድሜ 150 አመታት እንደ ሆነ ተናግረዋል።

አሣ እንደሌለው ፍጥረት አያንቀላፋም። ግን ያርፋል። አሣ ፀጥ ብሎ በሚተኛበት ጊዜ ዓይኑን አይጨፍንም። ምክንያቱም የዓይን ቆብ ስለሌለው ነው።

## ሸረሪት

በዓለም ትልቋ ሸረሪት የምትገኘው በጊያናስ ነው። ሶስት ኢንች ተኩል ርዝመት አላት። ከሸረሪት ዘር ሁሉ ትንሽቱ የአንድ ኢንች ሠላሳኛ ርዝመት አላት።

ሸረሪቶች በከፍተኛም ሆነ በዝቅተኛ ቦታ ለመኖር የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ 22.000 ጫማ ከፍታ ባለው ከኢቨረስት ተራራ ላይ ሸረሪቶች አሉ። ከምድር በታች ከማዕድን ዋሻዎችም ውስጥ የሚኖሩ አሉ።

በደቡብ አሜሪካ ያሉት ሸረሪቶች ከነከሱ ሰውን ይገላሉ።

## ጉንዳን

ስለ ጉንዳን ብዙ ታሪክ የለኝም። ግን ከጉንዳን ዘር ሁሉ ትልቁ የሚገኘው በደቡብ አሜሪካ መሆኑን አውቃለሁ። የደቡብ አሜሪካ ጉንዳኖች ርዝመታቸው 1.3 ኢንች ናቸው።

## ቁንጫ

የቁንጫ ታሪኳ ዝላይዋ ነው። ቁንጫዎች ሰባት ኢንች ይዘላሉ። ግን በ1910 ዓ.ም በካሊፎርኒያ በተደረገው የቁንጫዎች ዝላይ ውድድር አንዲት ቁንቻ 13 ኢንች በመዝለሏ አንደኛ ሆናለች። እስከዛሬም ሪኮርዷ አልተሰበረም። ቁንጫዎች ኃይለኛ እግር እንጂ ክንፍ የለአቸውም።

# ቢራቢሮ

የሕንዶች አትላስ የተባለው ቢራቢሮ የደቡብ አሜሪካኑ ቲሳኒያ የተባልቱ ቢራቢዎዎች ክንፎቻቸው 12 ኢንች ስፋት አለው። ግን በዓለም ላይ ካሉት ቢራቢሮዎች ሁሉ ትልቁ ያለው በኒውጊንያ ነው።

ቢራቢሮዎች ፈጣኖች ናቸው። ሌፒደፕቴራ የተባለው የመጨረሻው ትንሽ ቢራቢሮ በሰዓት 33 ማይል ይበራል። ይህን ቢራቢሮ ከቢራቢሮ ዘር ሁሉ የመጨረሻ ትንሽ ነው። በበራራ ግን ከሁሉ በላይ ነው።

# ጫካ (ዱር)

ብዙ ዕድሜ ያላቸውን ዱሮች ለማጥናት በተወሰደው እርምጃ መሠረት ዱሮቹን ያጠኑት ሳይንቲስቶች በ1955 ዓ.ም በየካቲት ወር አንድ መግለጫ አውጥተው ነበር። በመግለጫቸው እንደተመለከተው በሮዴሽያ ውስጥ የተገኘው ዱር ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሚሊዮን ዓመት ዕድሜ እንዳለው ገልጠዋል።

ከዚያ በፊት በ1953 ዓ.ም በኰሎራዶ ግዛት ውስት 65 ሚሊዮን ዓመታት ዕድሜ ያለው ዱር መገኘቱ ተገልጾ ነበር።

በዓለም ካሉት ጫካዎች ሁሉ በሰሜናዊ ሩስያ ያለውን የሚያህል ያለም። 2.700 ሚሊዮን ኤክርስ ስፋት አለው። በኛ አቆጣጠር 67.500.000 ጋሻ መሆኑ ነው።

# ዛፍ

በካሊፎርኒያ ሴኩአ በተባለ የሕዝብ መናፈሻ ውስጥ ጄኔራል ሼርማን ብለው የሰየሙት ዛፍ አለ። የዚህ ዛፍ ርዝመት 181 ክንድ ሲሆን ውፍረቱ 68 ክንድ ወይም 101 ጫማ ነው። ይህን ዛፍ ሰዎች ዙሪያውን ለማቀፍ ቢፈልጉ 17 ሰዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው መከበብ አለባቸው። የዚህ ዛፍ ክብደት 1320 ቶን እንደ ሆነ ይገመታል።

ከዛፎቹ ሁሉ ረጅሙ የሚገኘው በዚያው በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ ነው። ሐምበልት በተባለ የሕዝብ መናፈሻ «መሥራቹ ዛፍ» የሚሉት አንድ ዛፍ አለ። ዛፉ የተተከለው በ1930 ዓ.ም በተተከለ 26 ዓመቱ በ1956 ዓ.ም በኅዳር ወር ቁመቱ ቢለካ 242 ክንድ ሆነ።


ከዛፍ ሁሉ አሮጌው ወይ ሽማግሌው የሚገኘውም አሁንም በዚያው በካሊፎርኒያ ነው። አራት ሺህ ዓመታት ዕድሜ ያለው ነው።

ከዛፍ ዘር ባሕር ዛፍ በቶሎ ያድጋል። በተለይ በኡጋንዳና በመሐከለኛው አፍሪካ ያለው ባሕር ዛፍ ዘር ታዳጊ ነው። በሁለት ዓመት 30 ክንድ ያድጋል። ቀርከሀን ከዛፍ ዘር ካገባነው ከእሱ እኩል ታዳጊ የለም። በሴይሎን ያለው የቀርከሀ ዘር በቀን 16 ኢንች ያድጋል።

የማይድግ ደደብ ዛፍ ሲትካ የሚሉት ነው። ስለዚሁ የዛፍ ዘር ያጠኑት ሳይንቲስቶች እንደተናገሩት ሲትካ በ98 ዓመት ዕድሜ የሚያድገው አንድ ክንድ ብቻ ነው።

ከዛፍ ቅጠሎች ሁሉ ማስካሬኔ በተባለች ደሴት የሚገኘው ራፊያ የተባለው ዛፍ ቅጠሉ ይበልጣል። የቅጠሉ ርዝመት 42 ክንድ ሲሆን የጐኑ ስፋት ደግሞ ስምንት ክንድ ነው።

************



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸው። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)

6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY